**DSpace Institution**

**DSpace Repository** http://dspace.org

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2017-11-01

# þÿ è 8 › - M - Ê è - › K • K H p “ è % ë
# þÿ @ + ( e u • p “ ` ò 5 ` c ¨ p 5 p ó ð -
# þÿ p p ³ * • u ( u - u 5 p - 5 õ * ` ¨ J
# þÿ ë • u è @ ( ` )

þÿ ` % • , ` è •

http://hdl.handle.net/123456789/8195

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

# ምዕራፍ አንድ፦ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በስነልሳን፣ ድምፅ፣ ለስነድምፅ፣ ቃል፣ ለስነአገባብ መሠረታዊ አሀድ እንደሆነው ሁሉ ጥያቄም ለቋንቋ ፈተና መሠረታዊ አሀድ ነው (አገኘሁ፣ 2005)፡፡ እንደስነልሳን አሀድ ሁሉ ጥያቄንም መበየን አንዳንድ ጊዜ ከባድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መልስ አስመራጭና እውነት/ሀሰት ጥያቄዎች ቀላልና ልዩ ገፅታ ስላላቸው ማንም ሰው በቀላሉ ሊገነዘባቸው ሲችል፤ በአንፃሩ እንደቃለመጠይቅ፣ ሚና ነጠቃና ድርሰት ጥያቄዎች ውህዳዊ (integrative type) በመሆናቸው በቀላሉ ለመለየት ከባድ ናቸው፡፡ ውህዳዊ የቋንቋ ፈተና ስልት የተለያዩ የቋንቋ ችሎታዎችን ባንድ ጊዜ ለመመዘን የሚሞክር ነው፡፡ ሆኖም ጥያቄ፣ በፈተና ወቅት የተለየና (distinctive) ምሉዕ ትርጉም (meaningful) ያለው መረጃ የሚሰጥ አሀድ ነው (ብራውን፣ 1996)ን፤ እና ኦለር፣ 1979)ን ጠቅሰው አገኘሁ፣ (2005) እንደገለፁት።

ጥያቄ የፈተና መሠረታዊ አሀድ እንደመሆኑ መጠን ፈተናውን ለማሻሻል እያንዳንዱን ጥያቄ መገምገምና መከለስ ያስፈልጋል በማለት ብራውን (1996) እና ባችማን (1995) ይገልጻሉ፡፡ በማያያዝም የዚህ ዓይነት ጥንቃቄ የተሞላበት ግመገማ የጥያቄ ትንተና በመባል እንደሚታወቅና ይህም ስልታዊ ግምገማ የጥያቄ ውጤታማነትን በማረጋገጥ የተሻለውን ለመምረጥ የሚረዳ ሲሆን አራት የትንተና ዓይነቶች አሉ በማለት ያስረዳሉ። እነሱም፦ የጥያቄ አቀራረብ ትንተና (Item Format Analysis)፣ የክብደት ደረጃ ትንተና፣ የጥያቄ መለየት ችሎታ ትንተናና የአሳሳቾች ውጤታማነት ትንተና ናቸው፡፡ (ሁፍስ፣ 2003፤ ብራውን፣ 2004)፡፡ የጥያቄ ፎርማት ትንተና ትኩረት ጥያቄው በምን ያህል ትክክለኛነት እንደተጻፈና የተፈለገውን ይዘት ብቻ መለካቱን ማረጋገጥ ሲሆን ትንተናው የጥያቄ አቀራረብ ብቃት ላይ ውሳኔ መስጠት ነው (አልደርሰን እና ሌሎች 1995፤ ብራውን፣ 1996)፡፡

ግሮኑልድ (1968)፣ ብራውን (2004) እና ሃሊዲያናና ሌሎች (2002) እንደሚገልጹት እያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ዝርዝር ዓላማን ብቻ መለካት አለበት፡፡ አንዳንድ ጥያቄዎች ሰዋሰውንና ቃላትን በአንድ ጥያቄ አጣምረው ለመፈተን የሚዘጋጁ ቢሆኑም እነዚህን

ግልጽነት የጎደላቸው ጥያቄዎች (Impure items) በማለት ሂተን (1990) ይገልጿቸውና በአንድ ጥያቄ ውስጥ አንድ ባህሪ (feature) ብቻ መቅረብ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

መምህራን የጥያቄው አቀራረብ ከዓላማና ከጥያቄው ይዘት ጋር እንዲዛመድ ይፈልጋሉ፡፡ ይህም ማለት ትክክለኛውን የጥያቄ ዓይነት በመጠቀም መፈተን የተፈለገውን ነገር (ይዘት) ከፈተናው አቀራረብ መንገድና ዘዴ (modes) ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ነው በማለት ብራውን (1996) እና አልደርሰንና ሌሎች (1995) ያብራራሉ፡፡

አንድ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፣ የአንድ ትክክለኛ መልስ አስፈላጊነት ለአንድ ሰው ትክክለኛ የሆነው አማራጭ ለሌላው ትክክል ላይሆን ስለሚችልና በተመሳሳይ መምህራን ስህተት ነው ያሉት መልስ ለተወሰኑ ተማሪዎች ትክክል ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ስለሚኖር ነው (ብራውን፣ 1996፤ ብራዉን፣ 2004፤ ሂተን፣ 1990፤ እና አልደርሰንና ሌሎች፣ 1995)፡፡ ይህ አይነቱ ልዩነት የሚከሰተው ሰዎች አውዱን የሚረዱበት የተለያየ አመለካከት ስለሚኖራቸውና መምህራንም ትክክለኛ በተባለው መልስ ላይ ላይስማሙ የሚችሉ በመሆኑ ነው፡፡

የዚህ ችግር መነሻ የጥያቄ አዘጋጆች የተለያየ አመለካከት ሊፈጥሩ የሚችሉ ጥያቄዎችን ግምት ውስጥ ባለማስገባት ስለሚያዘጋጁና ይህንን ችግር በዘዴ ለመወጣትም የሚጠቀሙት መንገድ ይበልጥ ትክክለኛ መልስ እንዲመርጡ በማዘዝ ቢሆንም የዚህ ትዕዛዝ ችግር በፈተና አዘጋጆች እጅ ያለው መልስ ብቻ ለውሳኔ ማገልገሉና ምን ያህልስ ሥነ ምግባራዊ አቋም (ethical stance) አለው? የሚለው ነው በማለት ብራውን፣ (1996) እና ሁፍስ፣ 2003) ይጠይቁና ከዚህ ዓይነቱ ስህተት ለመጠበቅ አንድ ግልጽ የሆነ ትክክለኛ መልስ እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ይመክራሉ፡፡

በተጨማሪም ብራውን (1996) እንደገለጹት እያንዳንዱ ጥያቄ ከተማሪዎች ችሎታ ጋር ተቀራራቢ ሆኖ መጻፍ ይኖርበታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሂተን (1990) እንደሚያስረዱት ጥያቄውን ከተማሪው ችሎታ ጋር ተስማሚ ለማድረግ በጥያቄው ለመፈተን የተፈለገው ይዘት በጥያቄ አቀራረቡ ውስብስብነት የማይታይበት መሆን አለበት፡፡

በጥያቄ አቀራረብ ትንተና ትኩረት የሚያሻው ሌላው ነጥብ አሻሚ ቃላት (ambiguous terms) እና አሳሳች (tricky) የቋንቋ አጠቃቀም ማስወገድ ነው (ብራውን፣ 1996፤ ብራውን፣ 2004፤ ሃሊዲያናና ሌሎች፣ 2002 እና አልደርሰንና ሌሎች፣ (1995)፡፡ አክለውም

አሻሚና አሳሳች ቃላትን መጠቀም ተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ ቢያወቁትም የተሳሳተ መልስ እንዲሰጡ ምክንያት በመሆኑ ያልተፈለገ ውጤት እንደሚያስከትል ይገልጻሉ፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሃሊዲያናና ሌሎች (2002) እና ብራውን (1996) እንደሚያብራሩት አሉታዊና ጥምር አሉታዊ አገላለጾች ተፈታኞችን ባልተፈለገ ሁኔታ ግራ የሚያጋቡ በመሆናቸው በመሪ ጥያቄ ውስጥ መቅረብ የሌለባቸው ሲሆን የግድ ከሆነ ግን ከቃሉ ስር በማስመር ወይም አድምቆ (bold) በመጻፍ ምን መጠየቅ እንደተፈለገ ተማሪዎች ርግጠኛ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

በተመሳሳይ የፈተና አዘጋጆች፣ ተማሪዎች በአንድ ጥያቄ ውስጥ የሚገኘውን ፍንጭ ተጠቅመው ሌሎች ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችል አዘገጃጀትን ማስወገድ ሲሆን፣ ለአብነት በአንድ ጥያቄ ውስጥ የቀረበ ግልጽ ሰዋሰዋዊ መዋቅር ምሳሌን በመጠቀም ከፊት የሚያጋጥማቸውን ጥያቄ መመለስ ቢችሉ ተማሪዎቹ ጎበዝ ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን ወደኋላ ተመልሰው በቀደመው ጥያቄ ውስጥ የቀረበውን መረጃ (ፍንጭ) በመጠቀም ነው (አልደርሰንና ሌሎች፣ 1995 እና ብራውን፣ 1996)፡፡

ተማሪዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ቢያውቁም ጥያቄውና ምርጫዎቹ በተለያየ ገፅ ላይ በመቅረባቸው ብቻ ሊሳሳቱ ስለሚችሉ ሁሉም የጥያቄ ክፍሎች በአንድ ገፅ ላይ መጠቃለል እንደሚኖርባቸው (ብራውን፣ 1996) ያስረዳሉ፡፡

የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች የተነጠለ ዓረፍተ ነገርን (isolated sentence) ወይም ያልተሟላ ሀሳብን ከያዙ አሻሚና ግራ የሚያጋቡ ስለሚሆኑ ተስማሚና ሙሉ ትርጉም ያላቸው ጥያቄዎች ማዘጋጀት ይገባል (ሂተን 1990)፡፡ በተመሳሳይ ብራውን (2004) እንደሚያብራሩት አንዳንድ ጥያቄዎች ተገቢነት በሌላቸው በርካታ ቃላት የታጨቁ በመሆናቸው የጥያቄውን ግልፅነት ስለሚጎዱ ጥያቄዎቹም ሆኑ አማራጮቹ በተቻለ መጠን ቀላልና ግልፅ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንም ግልጋሎት የሌላቸውን ተጨማሪ መረጃዎች በማንበብ የተሰጣቸውን ጊዜ እንዳያባክኑና ያልተፈለገ ፍንጭ አግኝተው መልሱን በግምት እንዳይሰሩ ከሚዘጋጁት ጥያቄዎች ይዘት ጋር ምንም ተዛማጅነት የሌላቸውን መረጃዎች በማስወገድ በአንፃራዊነት ውጤታማ ጥያቄዎች እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል (ብራውን፣ 1996)፡፡

በጥያቄ ውስጥ የዘር፣ የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የብሔርና የቀለም ጉዳዮችን በማስወገድ አድሎአዊነትንና ወገናዊነትን የሚያመላክቱ የቃላት አጠቃቀም ፈፅሞ እንዳይካተቱ በዝግጅት ወቅት መጠንቀቅና ንቁ መሆን ይገባል (ብራውን፣ 1996)፡፡

የምርጫ ጥያቄዎች (Receptive response items) ከአፍልቆ ምላሽ ይልቅ ተማሪዎች ካዳመጡት ወይም ካነበቡት በመነሳት መልሶችን እንዲመርጡ የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎችም ሙሉ በሙሉ ተቀባይና (receptive) አስመራጭ (selective) ምላሽ ሰጪ ሲሆኑ እውነት/ሀሰትና የአዛምድ ጥያቄዎችም በዚሁ ስር ይመደባሉ (ብራውን፣ 1996 እና ብራውን 2004)፡፡

እያንዳንዱ የመልስ አስመራጭ ጥያቄ፣ የመሪ ጥያቄና (stem) ከሦስት እስከ አምስት የሚደርሱ አማራጮችን ሲይዝ ከአማራጮቹም አንዱ ብቻ ትክክለኛ መልስ ሲሆን ሌሎች አሳሳቾች ናቸው (ብራውን፣ 2004)፡፡ ሂተን (1990) በብራውን አገላለፅ በመስማማት አማራጮችን በተመለከተ ግን ከአምስት እስከሰባት አማራጮች ሊኖሩት ቢችሉም ሰባት ጥሩ አማራጮች ያሉት ጥያቄ ማዘጋጀት ፈታኝ ስለሚሆን ለክፍል ፈተና አራት አማራጮች ቢኖሩት የተሻለ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች በመጀመሪያ የጥያቄ ግንድ፣ በማስከተልም አማራጮችን ማለትም፣ ትክክለኛ መልስና አሳሳቾችን የሚይዙ ሲሆን፤ የአሳሳቾቹ ተግባር ተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ እስካላወቁ ድረስ በቀላሉ መልሱን እንዳያገኙ ትኩረታቸውን የሚስቡ ናቸው (ብራውን፣ 1996 እና ሃሊዲያናና ሌሎች፣ 2002)፡፡

በመልስ አስመራጭ ጥያቄ ዝግጅት ወቅት በአቀራረቡ ላይ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ለማሰወገድ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት እንደሚገባ ብራውን (1996)፤ ብራውን (2004) እና ግሮንሉድ (1968) ይመክራሉ፡፡ ያልታቀዱ ፍንጭ ሰጪዎች ተወግደዋል? ሁሉም አሳሳቾች ትክክለኛ መልስ ይመስላሉ? የማያስፈልጉ ድግግሞሾች ተወግደዋል? የአማራጮቹ አደራደር በጥንቃቄ ተጢነዋል? ወይም ትክክለኛ መልሶች ዘፈቀዳዊ አቀማመጥ ተከትለዋል? ከአሳሳቾቹ ‹‹መልሱ አልተሰጠም››፤ ‹‹ሁሉም መልስ ናቸው››፤ ‹‹ሀ እና ለ›› እና ‹‹ከ--ብቻ›› የሚሉት ተወግደዋል?

በአጠቃላይ እነዚህን መርሆዎች መሰረት በማድረግ ፈተና አለማዘጋጀት የፈተናውን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ይጎዳዋል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም በአዲስ አበባ ከተማ

አስተዳደር የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄ አቀራረብ (Item format) ትንተና ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

ፈተና ተማሪው ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘበ በመመዘን መረጃ የሚሰበሰብበትና የሚጠናቀርበት ነው፡፡ አልደርሰን (2004)ን በመጥቀስ አገኘሁ (2005) እንደገለጹት ብሔራዊ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ላይ የሚያሳድሯቸውን አሉታዊ ገጽታዎች በመመርመርና መፍትሄ በመፈለግ በትምህርት ጥራቱ ላይ የሚኖራቸውን ሚና ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡ ባችማን (1995) ፈተና ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ያላቸውን ችሎታ ለመለካት የሚያስችል በመሆኑ ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁ የተማሩትን ይዘቶች የሚወክሉ መሆን እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

ሁፍስ (2003) እንደሚገልጹት አንድ ፈተና ወደአንድ ተጨባጭ ወደሆነ ውሳኔ ለመድረስ የሚያስችል አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፈተና የተጠበቀውን ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው ጥያቄዎቹ የጥያቄ አዘገጃጀት መርሆችን በተከተለ መንገድ የተዘጋጁ እንደሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም ብራውን (2004) እና ግሪን (1998) እንደሚገልጹት ጥያቄዎች፣ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ለመሆናቸው ጥራትና ብቃታቸው በየጊዜው መገምገምና መተንተን ይኖርበታል፡፡ የጥያቄ ትንተናም ለፈተና አዘጋጆች የትኞቹ ጥያቄዎች ከፈተና መርህ አንፃር እንደተዘጋጁ መረጃ ይሰጣል፡፡

የጥያቄ አቀራረቡ ከፈተናው ዓላማና ከተፈታኞች መጠን አንፃር እንደሚለያይ በመግለጽ ብዙ ቁጥር ያላቸው ተፈታኞችን ለመፈተን የፈተናው አዘገጃጀት አማራጭ ሰጪ ጥያቄዎች ቢሆኑ ይመረጣል (ብራውን፣ 2004፤ ሁፍስ፣ 1992)፡፡ የምርጫ ጥያቄዎች ተተግባሪነትንና አስተማማኝነትን የሚያረጋግጡ፣ ጊዜ ቆጣቢ፣ ከአድሎ ነጻ፣ በርካታ ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ ለማቅረብ የሚያስችሉ፣ ለማረምና ለውጤት አመዘጋገብ የሚያመቹ ፣ ትክክለኛውን ምላሽ በቅድሚያ ማወቅ የሚያስችሉ፣ የመምህራንን የሥራ ጫና የሚቀንሱ በመሆናቸው ተመራጭ ያደርጋቸዋል፡፡

የፈተናውን ተገቢነት ለመገምገም የጥያቄ አቀራረብ ትንተና የእያንዳንዱን ጥያቄ ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ ለዚህም መልስ አስመራጭ ጥያቄዎች የፈተና አዘገጃጀት መርሆዎችን ተከትለው መዘጋጀት ይገባቸዋል ሲሉ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ (ግሮንሉድ 1968፤ ብራውን፣ 1996፤ ብራውን፣ 2004)፡፡ በተመሳሳይ በቋንቋ ፈተና ላይ ከሚደረገው ምርምር የሚገኘው መረጃ ተገቢ ፈተና ለማዘጋጀት እንደሚረዳ (ባችማን፣ 1995) ይገልጻሉ፡፡

ከ18 መማሪያ መጻሕፍት በሰበሰቧቸው 1080 መልስ አስመራጭ ጥያቄዎች የጥያቄ አቀራረብ ተገቢነት ላይ (ኢሊስዎርዝ፣ 1990) ባደረጉት ጥናት በአንድ ጥያቄ ውስጥ ከ3-4 መርሆዎች የተጣሱ ሲሆን፣ በአጠቃላይ 39.54% ጥያቄዎች ብቻ መርሆዎቹን ያሟሉና ሌሎች ጥያቄዎች ግን (60% ያክሉ) አንድና ከዛ በላይ መርሆዎችን መጣሳቸውን ይገልጻሉ፡፡ አክለውም አራት አማራጭ ካላቸው ጥያቄዎች ውስጥም የትክክለኛ መልስ ስርጭቱ በአብዛኛው ‹‹C›› (27.6%) ሲሆን፣ ከሌሎቹ አማራጮች በብዛት ትክክለኛ የመልስ አማራጭ በመሆኑ ለገማች ተማሪዎች ሰፊ እድል እንደሰጠም በጥናት ውጤታቸው አሳይተዋል፡፡

ሮድሪጌዝ (1977) የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አቀራረብ ተፅዕኖን በመረመሩበት ጥናታዊ ዘገባቸው ውስጥ አጠቃላይ የጥያቄ አጻጻፍ ዋና አላባውያን በሆኑት የመሪ ጥያቄ አጻጻፍና የአማራጮች አቀራረጽ በፈተናው ውጤት ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ አሳይተዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትም የጥያቄ መርሆዎችን ተከትለው ያልተዘጋጁ ጥያቄዎች በፈተና ውጤት ላይ ተፅዕኖ ማሳረፋቸውን፤ በመሪ ጥያቄ ውስጥ አሉታዊ አገላለፆች መኖራቸው ጥያቄዎችን ውስብስብ በማድረጋቸው የፈተናውን አስተማማኝነት መጉዳታቸውን፤ የምርጫ አዘገጃጀት ትክክለኛው መልስ ከአሳሳቾች ረዝሞ መገኘቱ ለግመታ (gussing) መልስ አመቺ መሆናቸውን አመላክቷል፡፡ በማያያዝም በጥያቄ አቀራረብ ላይ የሚደረጉ በምርምር ላይ የተመሰረቱ ትንተናዎች የፈተና ጥራትን ለማሳደግ ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል (ሮድሪጌዝ፣ 1977)፡፡

ሃላዲያናና ዶዊኒንግ (1986) በጥያቄ አጻጻፍና ፈተና አዘገጃጀት ላይ ያላቸውን አንድምታ ለመፈተሽ ሁለት፣ ሦስትና አራት አሳሳቾች ያሏቸው ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ ምርምር ያካሄዱ ሲሆን፣ ሦስት አሳሳቾችን የያዙ የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች በከፍተኛ ደረጃ

ውጤታማ (highly efficient) እና ለጊዜ አጠቃቀም አመቺ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን ለመልስ የቀረቡ አሳሳቾችን በማዘጋጀት ረገድ ተገቢው ጥንቃቄ ካልተደረገ ግን የፈተናውን ውጤት እንደሚጎዳ ሃላዲያናና ዶዊኒንግ (1986) በጥናታቸው ውጤት አመላክተዋል፡፡ ከላይ የቀረቡት የውጪ ሀገር ተመራማሪዎች ጥናቶችም ቢሆኑ የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አቀራረብን ለመገምገም መርሆዎችን በተናጠል በመውሰድ የተካሄዱ ናቸው፡፡

ትንሳኤ (1988) የአማርኛ ቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት በሚል ርዕስ ባቀረበው የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናዎች ተገቢ ወይም ጥሩ የመመዘኛ መሳሪያ መሆናቸውና አለመሆናቸውን መርምሯል፡፡ በጥናቱም ከተገቢነት አንጻር አብዛኛዎቹ የቃላት ፈተናዎች መማሪያ መጽሐፍቱን መሰረት ያላደረጉና ከአስተማማኝነታቸውም አንፃር ደረጃቸው ዝቅተኛ እደሆኑ በጥናቱ ውጤት ላይ አመልክቷል፡፡

ባንችአምላክ (2002) የ2001 ዓ.ም የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና የይዘት ትክክለኝነት ብቃት ትንተና በሚለው ጥናታዊ ርዕስ የፈተናውን ይዘታዊ ተገቢነት ለመመርመር በተደረገው ጥረት የትምህርቱን ይዘት ሆነ አላማን አስመልክቶ መዘጋጀት የሚገባውና የተዘጋጀው የጥያቄ መጠን የማይጣጣም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ፈተናው የትምህርት ይዘታዊ ተገቢነትን በብቃት የማሟላት ደረጃው ዝቅተኛ መሆኑን አሳይታለች፡፡

ቅጣው የ2006 ዓ.ም የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ብቃት /item format/ ከምርጫ ፈተና አዘገጃጀት መርሆች አንፃር መዘጋጀታቸውን በገመገሙበት ጥናት ውስጥ አምስት የሚሆኑ ጥያቄዎች መርሆዎቹን ያልተከተሉ መሆናቸውን ገልጸዋል (ቅጣው፣ 2007)። ከዚህ አንጻር በተመሳሳይ መልኩ በክልላዊው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥያቄዎች የጥያቄ አቀራረብም የምርጫ ጥያቄ አዘገጃጀት መርሆዎችን አልጠበቁ ይሆን? የሚል ጥያቄ ተመራማሪው እንዲያነሳ ምክንያት ሆኖታል፡፡

ሌላዉ አጥኚው በ2007 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ከ1ኛ-8ኛ ክፍሎች አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት የማስማማት ሥራ ላይ ከተለያየዩ ትምህርት ቤቶች ከተውጣጡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ከክልሉ የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች ጋር አብሮ የመሥራት አጋጣሚ ስላገኘ

በመስተዳደሩ በሚዘጋጀው የስምንተኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና አዘገጃጀት ላይ ችግር መኖሩንና የፈተናው ውጤትም ከመጠነ ማለፍና መውደቅ ጋር በተያያዘ ከሚሰራ ትንተና ባለፈ በጥያቄ አቀራረብ ትንተና (item format ) ላይ የተሠራ የሀገር ውስጥ ጥናት ከተቃኙት መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም በፈተናው ጥያቄዎች ላይም ከተማሪዎችና ከመምህራን በተለያዩ ጊዜያት ተደጋጋሚ ጥያቄዎች የሚነሱ በመሆኑ ምናልባት ይህ ችግር ከጥያቄ አቀራረብ ጋር የተያያዘ ይሆን? የሚለው ጥያቄ ጥናቱን ለማድረግ አጥኚውን አነሳስቶታል፡፡ በመሆኑም በጥናቱ የሚከተሉት ቁልፍ ጥያቄዎች ምላሽ ያገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና መሪ ጥያቄዎች ከጥያቄ አቀራረብ አንፃር ምን ያህል መርሆዎችን የተከተሉ ናቸው?
2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄዎቹ አማራጮች፣ የአማራጮች አቀራረብን ምን ያህል ያሟላሉ?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ የጥያቄ አቀራረብን (item format analysis) መተንተን ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና መሪ ጥያቄዎች ከጥያቄ አቀራረብ መርሆ አንፃር ተገቢነታቸውን መመርመር፣
2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄ አማራጮች ምን ያህል የአማራጮች አቀራረብን የጠበቁ መሆናቸውን መፈተሽ፣

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚህ ጥናት ትኩረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄ አቀራረብን (item format analysis) መገምገም ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤት ለክልላዊ ፈተና አዘጋጆችና ለትምህርት ባለሙያዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

1. ፈተና አዘጋጆች የመልስ አስመራጭ የጥያቄ አቀራረብ መርሆን ተከትለው የሚያወጧቸው ፈተናዎች ለመማር ማስተማሩ ተግባር አጋዥ መሆኑን ተገንዝበው ፈተናውን እንዲያዘጋጁ ይረዳል፣
2. ጥያቄዎችን በመገመገም የሚገኘውን መረጃ በመጠቀም በተከታታይ የሚዘጋጁ ፈተናዎች የጥራት ጉድለት እንዳይታይባቸው ለመፈተሽ ሊያነሳሳ ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡
3. እንዲሁም ለሌሎች መሰል ጥናቶች መነሻ በመሆን አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄ አቀራረብ ትንተና ላይ ያተኩራል፡፡ በጥናቱ ከ2005-2007 ዓ.ም ድረስ ለ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና የቀረቡ የሦስት ተከታታይ አመታት ፈተናዎች ይገመገማሉ፡፡ ፈተናው ሙሉ በሙሉ የቀረበው በመልስ አስመራጭ በመሆኑ ሌሎች የጥያቄ አቀራረብ አይነቶችን አይመለከትም፡፡

የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ፈተናዎቹ ከሁለት አጠቃላይ መርሆዎች አንፃር ይተነተናሉ፡፡ የመጀመሪያው መርህ *የመሪ ጥያቄ አቀራረብ ትንተና* ነው፡፡ በዚህም መሪ ጥያቄው፡- ግልፅና በቂ መረጃ ስለመያዙ፣ ካላስፈላጊ መረጃዎችና የቃላት ክምችት የጸዳ ስለመሆኑ፣ በአዎንታዊ አቀራረብ ስለመጻፉና የአሉታዊ ቃላት አጠቃቀሙ ተገቢነት፣ ፍንጭ ሰጪ ስላለመሆኑ፣ የአጻጻፍ ስልት፣ የሰዋሰው፣ የሥርዓተነጥብና የሆሄያት ሁኔታና አቀማመጥ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ ከሚሉት ነጥቦች አንጻር የሚታይ ይሆናል (ሃሊድያና፣ ዶውኒንግ እና ሮድሩጌዝ፣ 2002፤ ግሮንሉንድ፣ 1988 እና ብራውን፣ 1996)፡፡

ሁለተኛው መርህ *የአማራጮች አቀራረብ ትንተና* ሲሆን ትኩረቱ በቀረቡት አማራጮች ላይ ይሆናል፡፡ የመተንተኛ መስፈርቶቹም አሳሳቾች የሚስቡና ተአማኒነት ያላቸው ስለመሆናቸው ወይም ሁሉም አሳሳቾች ትክክለኛ መልስ ስለመምሰላቸው፣ አማራጮቹ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲኖራቸው ተደርገው ስለመቀረጻቸው፣ የማያስፈልጉ ድግግሞሾች ስላለመኖራቸው፣ የአማራጮቹ አደራደር በጥንቃቄ ስለመጤናቸው፣ "መልስ አልተሰጠም" እና "ሁሉም መልስ ናቸው" የሚሉት በአማራጮች ውስጥ ስላለመኖራቸው፣ ፍጹም መለያ የሆኑ ቃላት በአሳሳቾቹ ውስጥ ጥቅም ላይ ስላለመዋላቸው፣ የመሪ ጥያቄና የአማራጮች አጻጻፍ ስልት ተገቢነታቸው በፈተና አቀራረብ ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ በዘርፉ ምሁራን ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ በግምገማው የሚዳሰሱ ይሆናሉ (ሃሊድያና፣ዶውኒንግ እና ሮድሩጌዝ፣ 2002፤ ግሮንሉንድ፣ 1988 እና ብራውን፣ 1996)፡፡

## 1.6 የቁልፍ ቃላት ብያኔ

በዚህ ጥናት የጥያቄ አቀራረብ ትንተና፣ የአማራጮች አቀራረብ ትንተናና የፈተና መርሆ የሚሉት ቁልፍ ፅንሰሀሳቦች ናቸው፡፡ ተግባራዊ ብያኔያቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*የጥያቄ አቀራረብ ትንተና (item format analysis)፡-* ለፈተና የቀረበውን መሪ ጥያቄ በጥናቱ ወሰን ውስጥ በተገለጹት መስፈርቶች መሰረት መዘጋጀታቸውን ለመፈተሽ የሚደረግ የመሪ ጥያቄዎች ግምገማን ወይም ትንተናን የሚመለከት ነው፡፡

*የአማራጮች አቀራረብ ትንተና (receptive response items)፡-* ለመሪ ጥያቄ ምላሽ ይሆናሉ ተብለው የቀረቡትን አማራጮች ማለትም ትክክለኛውን መልስና አሳሳቾችን በጥናቱ ወሰን ውስጥ ከቀረቡት መርሆዎች አንፃር ለመፈተሽ የሚደረግ የአማራጮች ግምገማን ወይም ትንተናን የሚመለከት ነው፡፡

*የፈተና አጻጻፍ መርሆ፡-* መሪ ጥያቄዎችንና አማራጮችን ለመተንተን የሚያገለግል መስፈርት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት ፡- ክለሣ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ ፈተና ምንነት

እንደዘርፉ ምሁራን ገለጻ የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች የተረዱዋቸውን የቋንቋ ይዘቶች በትክክል መጨበጣቸውንና አለመጨበጣቸውን ለማወቅ የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡ ብራውን፣ (1987) እንደሚያሰረዱት ፈተና በአንድ የተወሰነ የትምህርት ሂደት የተማሪውን ችሎታና እውቀት ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡ አክለውም ስለፈተና ምንነት ሲነሳ ሁለት የማይነጣጠሉ ፅንሰሃሳቦች መኖራቸውን ይገልጻሉ፡፡ የመጀመሪያው የፈተና ዘዴ ሲሆን፣ ይህ ሃሳብ ፈተና መሳሪያ ሆኖ ተፈታኙ መልስ የሚሰጥበት ክህሎት ነው፡፡ ሁለተኛው ፈተና መለኪያ ነው የሚለው ጽንሰሀሳብ ሲሆን፣ አንዳንድ ፈተናዎች የተፈታኙን አጠቃላይ ችሎታ ሲለኩ የተቀሩት ደግሞ የተወሰኑ ክሂሎችን ለመለካት የሚያገለግሉ የመለኪያ መሳሪያዎች ተደርገው መወሰዳቸውን የሚመለከት ነው (ብራውን፣ 1987)፡፡

ፈተና የተማሪውን የእውቀት ደረጃ እስከምን እንደሆነ ለማወቅ መረጃ የሚሰበሰብበትና የሚቀናጅበት ነው (ቤከር፣ 1989)፡፡ በተመሳሳይ ባችማን (1995) እንደሚገልጹት ፈተና የተማሪዎችን ቋንቋ መሻሻል ለመገምገም፣ በየትኛው የቋንቋ ክሂልና የእውቀት ዘርፍ ድክመት እንዳለባቸው ለመጠቆም፣ የትኛውን የትምህርት ይዘት ትኩረት ሰጥተው እንደሰሩ ለመለየትና፣ የመምህራንን የትምህርት አቀራረብ ለመፈተሽ የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡

ፈተና ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የሚጠቁም መሳሪያ ነው በማለት ሃሪሰን (1983) ይገልጻሉ፡፡ አያይዘው እንደሚያስረዱት መምህራን ምን ዓይነት ክንውኖች ለመማር ማስተማር አስፈላጊ እንደሆኑ፣ ቀደም ሲል ከተከናወኑት ተከታታይ ክንውኖች የትኞቹ ተማሪዎችን ለውጤት እንዳበቁ ይጠቁማቸዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሊያዳብሩት የሚገባ አመለካከትን፣ በመማር ማስተማር ሂደቱ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ መወሰድ የሚገባቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች ለመውሰድ የሚያስችሉ መረጃዎችን ያስገኙላቸዋል፡፡ መረጃውን በመጠቀምም ተማሪው ደካማና ጠንካራ ጎኑን ለመፈተሽና ከፈተናው በሚገኘው ውጤት የመማር ተነሳሽነቱን ለማጠናከር ምጋቤምላሽ (feed back) ያገኝበታል (እንደሃሪሰን፣ 1983) ገለጻ፡፡

በተመሳሳይ ብራውን (2004) የቋንቋ ፈተና በተማሪዎች ላይ የታየውን እድገትና መሻሻል ለመከታተል፣ በቋንቋ ትምህርቱ ለተስተዋሉ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት፣ የመማር ማስተማር ሂደት ስኬታማ ለማድረግና ሥርዓተ ትምህርቱን ለመገምገምና የሚያገለግል መሳሪያ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

ተማሪዎች ከቀረበላቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ያዳበሩትን የእውቀት፣ የግንዛቤና የክህሎት ለውጦች ምን ደረጃ እንደሚገኙ ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ ነው ሃበርድ እና ሌሎች (1983) እንደገለጹት ፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደት የተገኘውን የአሰራር ለውጥና የተካበተውን እውቀት መመዘን የቋንቋ ፈተና ዋና ትኩረት እንደሆነ ሪቻርደስ፣ (1998) ያስረዳሉ፡፡

## 2.2 የቋንቋ ፈተና ዓላማ

የቋንቋ ፈተና ዓላማ እንደሚዘጋጀው ፈተና አይነትና እንደፈተናው አቀራረብ የተለያየ ቢሆንም በተማሪዎች መካከል የሚታየውን ልዩነት ለመለካት፣ አስቀድሞ የታቀደው የቋንቋ ትምህርት እንደታለመው ከግብ መድረስ መቻሉን ለማረጋገጥ እንዲሁም በፈተናው የሚገኘውን መረጃ በመጠቀም የትምህርት አቀራረቡን፣ የማስተማር ዘዴውንና የትምህርት መሳሪያውን ማሻሻል ነው በማለት ግሮንሉንድ፣ (1981) ይገልጻሉ፡፡

እንደባችማን (1990) ገለጻ የቋንቋ ፈተና ዓላማ የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ መለካት፣ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ ማረጋገጥ፣ የተማሪዎችን ጥንካሬና ድክመት ማሳየት፣ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ላይ ማሻሻያና ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ መስጠት እና የትምህርት ዓላማዎቹ ምን ያህል እንደተሳኩ ማመልከት ናቸው፡፡

## 2.3 የቋንቋ ትምህርትና የቋንቋ ፈተና ተዛምዶ

ጆን ብራይት (1968) ቀደም ባሉት ጊዜያት ፈተናን ከማስተማር ነጥሎ የማየት ዝንባሌ መኖሩን ይገልጹና ነገር ግን ማስተማርና መፈተን ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውና አንዱ ያለሌላው ሊታሰብ የማይችል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ፈተና የመማር ማስተማር አካል በመሆን ተማሪዎች በቀጣይ ምን ማሻሻል እንዳለባቸው ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል በማለት (ላምበርት እና ላይንስ፣2000)ን በመጥቀስ (ቻን ዮዋን እና ካኡር፣ 2013) ይገልጻሉ፡፡ የትምህርት ቤቶች ዋና ዓላማ የተማሪዎችን ትምህርት ማሳደግ መሆኑን ጠቅሰው ፈተና ወይም ምዘና የዚህ ሂደት ማዕከል መሆኑን ያብራራሉ (ቻን ዮዋን እና ካኡር፣ 2013)፡፡

ፈተና ሲዘጋጅ በቅድሚያ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት ወይም የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ብቃት በመለካት ለማሻሻል የሚረዳ ግብዓት ለማግኘት መሆን ይገባዋል በማለት ሂተን፣ (1975) ያስረዳሉ፡፡

ፈተና የትምህርቱን ዓላማ መለካት እንዳለበት ይገልጹና የሚቀርቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ከትምህርቱ ያገኙትን የዕውቀት ደረጃ ለመለካት ተስማሚ መሆን እንዳለባቸው ቤን ክሌይ፣ (2001) ይገልጻሉ፡፡

እንደስቲፈን አንድሪው (2004) አገላለጽ ፈተና ምን ትምህርት ተሰጠ፣ እንዴት ተሰጠ፣ ተማሪዎች ምን ተማሩ እና እንዴት ተማሩ ለሚለው መረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት መማር ማስተማርን አስመልክቶ የቋንቋ ፈተና ጠቃሚ የመረጃ ምንጭ ነው፡፡ ከቋንቋ ፈተና የሚገኘው መረጃ ቋንቋን ለማስተማር ጥቅም ላይ የዋለው ስነዘዴና (Method) አቀራረብ (Approach) ውጤታማነትን ለመገምገም ያስችላል (ባችማን፣1995)፡፡

በተጨማሪም ባችማን (1995) የቋንቋ ፈተና የሚከተሉት ሁለት ጥቅሞች እንዳሉት ይገልጻሉ፡፡ የመጀመሪያው የትምህርት ፕሮግራሙን አስመልክቶ ውሳኔ ለማስተላለፍ የሚረዳ የመረጃ ምንጭ መሆኑን እና ሁለተኛው ቋንቋን በማስተማር ሂደት፣ በቋንቋና በቋንቋ ለመዳ ላይ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ ፍንጭ ይሰጣል በማለት ገልጸዋል፡፡

ጥሩ ፈተና የማስተማሩን ሥራ ስለሚያሻሽል ለቋንቋ ትምህርቱ አገልጋይ ነው በማለት (ዴቪስ፣ 1968) የገለጹትን ሃሳብ በመጥቀስ በቋንቋ ፈተናና በቋንቋ ትምህርት መካከል ያለው ግኑኝነት የጋራነት (partenership) እንጂ የአገልጋይነት እንዳልሆነ (ሁፍስ፣ 2003) ያስረዳሉ፡፡

የቋንቋ ፈተና ለቋንቋ ትምህርቱ ሁለት ዕድሎችን ለመስጠት ያለመ መሆኑን ገልጸው አንደኛው ለሚፈተኑት ተማሪዎች ሲሆን ሁለተኛው ፈተናውን ለሚፈትኑት መምህራን ነው

በማለት (ብሬይን ቶሞሊንሰን፣ 2005) ይገልጻሉ፡፡ እንደብሬይን ቶሞሊንሰን (2005) አገላለጽ ተማሪዎች፣ ለፈተና በሚዘጋጁበት ጊዜ ከመምህራኖቻቸው ጋርና በተናጠል በግላቸው ከፈተናው በፊት ምን እንደሰሩ ለማወቅ ይረዳቸዋል፤ በፈተና ጊዜ የሚያውቁትንና ማድረግ (ማከናወን) የሚችሉትን ለመረዳት ዕድል ይሰጣቸዋል፤ ከግል ዕብረቃቸውና ከመምህራኖቻቸው ምጋቤ ምላሽ ለማግኘት ይረዳቸዋል፡፡

መምህራን ከቋንቋ ፈተናው ስለሚያገኙት ጥቅም ሲገልጹም፣ በታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች ምን እንዳወቁና ምን እንዳላወቁ ይለዩበታል፤ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ምን መሻሻል እንዳሳዩ ይለዩበታል፤ ትምህርቱ በተማሪዎች ላይ ያመጣውን ተፅዕኖ (effect) ለመረዳት የሚያስችላቸውን መረጃዎች ያገኛሉ (ብሬይን ቶሞሊንሰን፣ 2005)፡፡

በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የቋንቋ ፈተናው ተፅዕኖ ጠቃሚ ወይም ጎጂ ሊሆን እንደሚችልና የፈተናው ይዘትና ቴክኒክ ከቋንቋው ኮርስ ዓላማ ጋር ልዩነት ካለው በቋንቋ ትምህርት ላይ ጉዳት እንደሚያስከትል (ሁፍስ፣ 2003) ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይ ብሬይን ቶሞሊንሰን (2005) በተለይ በዓለም አቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ የቋንቋ ፈተናዎች፣ ተማሪዎች ለፈተናው በሚያደርጉት ዝግጅት ለተግባቦት የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ መሆኑን የቋንቋ መምህራን እንደድክመት በማንሳት እንደሚሞግቱ ገልጸዋል፡፡

በርካታ ቁጥር ላላቸው ተማሪዎች የሚዘጋጁ የቋንቋ ፈተናዎች ለተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፋይዳ አነስተኛ እንደሆነና ለዚህም ዝግጅቱን ጨምሮ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ያለው ዕድል አነስተኛ ነው በማለት (ባችማን፣ 1995) ይገልጻሉ፡፡ በተመሳሳይ ብሬይን ቶሞሊንሰን (2005) በማጠቃለያ ፈተናዎች ምግቤ ምላሽ የማይሰጥ መሆኑን ገልጸው መፍትሄው ተማሪዎች በግላቸው ማጣቀሻ መጻሕፍትን በመጠቀም ወይም ርስ በርሳቸው ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጣጡ መርዳት ይገባል ይላሉ፡፡

## 2.4 የመልስ አስመራጭ ጥያቄ ክፍሎች

የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ችግሩን የያዘው *መሪ ጥያቄ*፣ ትክክለኛ ያልሆኑ መልሶች የያዙ አማራጮችን *አሳሳቾች* እና ከተሰጡት አማራጮች አንዱ በመሪ ጥያቄው ውስጥ ለቀረበው ችግር መፍትሄ የሆነው *ትክክለኛ መልስ* በማለት (ዶውን ዚማሮ፣ 2004) በሦስት ክፍሎች ይመድቡዋቸዋል፡፡

የመልስ አስመራጭ ጥያቄ የመጀመሪያው ክፍል መሪ ጥያቄ ሲባል ቀጥለው የሚመጡት አማራጮች ናቸው በማለት (ሂተን፣ 1988፤ በርተንና ሌሎች፣1991፤ ብሬም፣ 2013) በሁለት ይመድቧቸዋል፡፡ ከአማራጮቹ አንዱ መልስ ወይም ትክክለኛ አማራጭ ነው፡፡ ቀሪዎቹ አማራጮች አሳሳቾች ሲሆኑ በመሪ ጥያቄ ለቀረበው ችግር ትክክለኛውን ምላሽ የማያውቁ ተማሪዎችን እንዲያሣሥቱ የቀረቡ ናቸው (ሂተን፣ 1988፤ በርተንና ሌሎች፣1991፤ ብሬም፣ 2013)፡፡

መልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ተፈታኞች ከቀረቡላቸው አማራጮች ትክክለኛውን መልስ እንዲመርጡ የሚጋብዝ ነው፡፡ ሁሉም ጥያቄዎች መሪ ጥያቄ ያላቸው ሲሆን በአብዛኛው ከሦስት አስከ አምስት አማራጮችን ይይዛሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ መልስ ሲሆን ሌሎች አሳሳቾች ናቸው (ብራውን፣ 2004) ፡፡

## 2.5 የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ጠንካራ ጎኖች

የመልስ አስመራጭ ጥያቄን ለመመለስ ከሚወስደው ጊዜ አንፃር ሰፋ ያለ የይዘት ሽፋንን ለመፈተን ይጠቅማል፡፡ ከሌሎች የምርጫ ጥያቄዎች (እውነት ሀሰትና አዛምድ ጥያቄዎች) አንፃርም የይዘት ተገቢነት (content validity) ለማረጋገጥ እንደሚጠቅም (ዴቪድ ታነር፣ 2003) ይገልጻሉ፡፡ የመልስ አስመራጭ ጥያቄ በፈተና እርማት፣ ውጤት አመዘጋገብና አያያዝ ላይ አጭር ምላሽ ከሚሹና በጽሁፍ ከሚመለሱ ጥያቄዎች በተሻለ አስተማማኝ ነው (ዴቪድ ታነር፣ 2003)፡፡

ክለግና ካሽን (1986) እንደሚገልጹት ስፋት ያለው የመማር ግቦችን ለመፈተን የሚያስችሉ ሁለገብ ባህሪ ያላቸው በማለት የሚከተሉትን ነጥቦች ይዘረዝራሉ፡፡ የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች፣ ሁሉንም ዓይነት የእውቀት ደረጃዎች ከቀላል የትውስታ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የአስተሳሰብ ደረጃ (መተግበር፣ መተንተንና መገምገም) ለመፈተን ያስችላሉ፤ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ማቀነባበር ወይም ማቀናጀት መቻላቸውን መመዘን ያስችላሉ፤ ትክክለኛ ያልሆኑ መልሶች ወይም አሳሳቾች በበርካታ ወይም በሁሉም ተማሪዎች ከተመረጡ የተማሪዎችን የመማር ችግር ለመለየት የመረጃ ምንጭ ስለሚሆኑ ለመምህሩና ለተማሪው የምጋቤ ምላሽ ግብዓት ይሆናሉ (ሂተን፣ 1988)፤ በርካታ ጥያቄዎችን ማቅረብ ስለሚቻል የትምህርቱን ናሙናዎች መፈተን ያስችላሉ፤ ተማሪዎች

ጥያቄዎቹን በአንፃራዊነት በአነስተኛ ጊዜ እንዲመልሱ ዕድል ይሰጣሉ፤ በማሽንም ሆነ በሰው ለማረም ያመቻሉ በማለት ክለግና ካሽን፣ (1986) ያስረዳሉ፡፡

የመልስ አስመራጭ ጥያቄ ከሁለገብነት (Versatility)፣ ከአስተማማኝነት (Reliability) እና ከትክክለኛነት (Validity) አንፃር ውጤታማና ጠቃሚ የፈተና መንገድ ነው (እንደብሬም፣ 2013) ገለጻ::

ብሬም (2013) እንደሚገልጹት ሁለገብነት፣ በመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ከቀላል የማስታወስ ደረጃ እስከ ትግበራ፣ ትንተና ግምገማ ያሉ ልዩ ልዩ የዕውቀት ደረጃዎችንና የመማር ግቦችን ለመለካት ያስችላሉ:: በርተንና ሌሎች (1991) ክስተቶችን መተንተንን፣ መርሆችንና አዳዲስ ሁነቶችን መተግበርን፣ ፅንሰ ሃሳቦችን መረዳትን፣ በእውነታና በግለሃሳብ መካከል መለየት መቻልን፣ የምክንያትና ውጤት ተዛምዶን መተርጎምን፣ ቻርቶችንና ካርታዎችን መተርጎምንና ማንበብን፣ የመረጃ ትክክለኛነትን መዳኘትን እና ችግሮችን መፍታትን በመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች መፈተን መቻሉን ያነሳሉ፡፡

አስተማማኝነትን አስመልክቶም የምርጫ ጥያቄዎች እርማት ከአራሚው ተፅዕኖ ነፃ መሆኑና በተለይ ጥያቄዎቹ አንድ የትምህርት ዓላማ ለመጠየቅ ብቻ የተዘጋጁ ከሆኑ አስተማማኝነቱ ወጥነት እንዲኖረው ያደርጋል በማለት ብሬም (2013) ይገልጻሉ፡፡

የፈተና ብቃትና የውጤት ተቀባይነት የትክክለኛነት መገለጫ ነው (ብሬም፣ 2013)፡፡ የፈተና ትክክለኛነት በታቀደው መሰረት ሊለካ የተፈለገውን የመዘነ እንደሆነ ነው በማለት ብራውን፣ (1994) እና ሃሪሰን፣ (1983) ይገልጻሉ፡፡ የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ሰፊ ይዘትን ለመሸፈን የሚያስችል ወካይ ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት አመቺ ስለሆኑ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ዕድል ይሰጣሉ (ብሬም፣ 2013 እና በርተንና ሌሎች፣1991)፡፡

የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ፈተና ጠንካራ ጎኖች በማለት ዚማሮ (2004) ከቀላል እስከ ውስብስብ የመማር ግቦችንና ሰፊ የችሎታ መለኪያ ናሙናዎችን በማቅረብ መለካት ያስችላሉ፤ በጥብቅ የተደራጁ፣ የተዋቀሩና ግልፅ ጥያቄዎችን ማቅረብ ያስችላሉ፤ አሳሳቾች ምርመራዊ የመረጃ ምንጭ (diagnostic information) ይሆናሉ፤ በግምት ለመመለስ ያላቸው እድል ከእውነት ሀሰት ጥያቄዎች ያነሰና እርማቱ ከድርሰት (essay) ፈተናዎች አስተማማኝነት ያለው ነው፤ የጥያቄዎቹን የክብደት መጠንና (difficulty level) የመለየት አቅም (discrimination power) ለመተንተን ምቹ ናቸው፤ በአብዛኛው ለአንድ ጥያቄ አንድ

ደቂቃ ስለሚሰጥ በርካታ ጥያቄዎችን በአንፃራዊነት በአጭር ጊዜ መፈተን ያስችላሉ ይዘረዝራሉ፡፡

## 2.6 የመልስ አስመራጭ ጥያቄ ውስንነቶች

ለመልስ የቀረቡ በቂ አሳሳቾችን ማቅረቡ ወይም መቅረፁ ቀላል ተግባር ባለመሆኑ የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ከባድ ያደርገዋል በማለት (ቤን ክሌይ፣2001) ይገልፁና ከዚህም የተነሳ ዝግጅቱ ሰፊ ጊዜን ይወስዳል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከላይ በቤን ክሌይ ከተገለፁት ነጥቦች በተጨማሪ ለተፈታኞች ምላሾቻቸውን በማደራጀት ሃሳባቸውን ለመግለፅ ዕድል የማይሰጡ መሆናቸውን፣ ውጤቱ በንባብ ችሎታ የሚወሰን መሆኑ፣ አልፎ አልፎ ከአንድ በላይ ትክክለኛ መልሶች ሊገኙ መቻላቸውን እና በርካታ ጥያቄዎችን ከመያዙ የተነሳ እያንዳንዱ ተማሪ ለምን የተሳሳተ መልስ እንደመረጠ ለመወሰን ይከብዳል በማለት የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ድክመትን (ዚማሮ፣ 2004) ያስረዳሉ፡፡

በመልስ አስመራጭ ጥያቄ ገለፃ ማድረግን፣ ምሳሌ መስጠትን፣ ተግባርን በማከናወን ወይም በድርጊት ማሳየትን እና የግል ሃሳብን በፅሁፍ ማንፀባረቅን መለካት አለመቻሉን በውስንነት ይጠቅሳሉ (ብሩቱንና ሌሎች፣ 1991)፡፡

በእውናዊው ዓለም ተግባቦትን አስመልክቶ የቋንቋ አጠቃቀም ከቀረቡት አማራጮች የሚመረጥ ሳይሆን በአውዱ ውስጥ በመሆን በአፍልቆት የሚከወን ተግባር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ዋነኛ ድክመት ቋንቋን ከተግባቦት አንጻር ለመለካት የማይስችል መሆኑን (ሂተን፣ 1988) ይገልጻሉ፡፡

## 2.7 የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አቀራረቦች

*ሀ) አንድ ነጠላ መልስ*

ይህ የጥያቄ አቀራረብ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ አንዱ ብቻ ትክክለኛ መልስ የሚሆንበት አቀራረብ ነው (በርተንና ሌሎች፣ 1991 እና ብራን፣ 1994)፡፡

*ለ) የተሻለ መልስ*

ሁሉም የቀረቡት አማራጮች በመሪ ጥያቄው ለቀረበው ችግር ወይም ተግባር መፍትሄ ወይም መልስ መሆን የሚችሉ ሆነው አንዱ ግን ከሁሉም እጅግ የቀረበና የተሻለ መልስ (best answer) ሊሆን የሚችልበት የጥያቄ አቀራረብ ነው (ግሩኖልድ፣ 2003 እና በርተንና ሌሎች፣ 1991)፡፡

*ሐ) አሉታዊ አቀራረብ*

በዚህ የጥያቄ አቀራረፅ ተማሪዎች ትክክለኛ ያልሆነውን ምላሽ እንዲመርጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከባለአራት አማራጭ ጥያቄ ሦስቱ በመሪ ጥያቄው ለቀረበው ችግር ትክክለኛ መፍትሄ ሆነው በቀረጹም መልስ መሆን አይችሉም፡፡ ቀሪው አንዱ ትክክለኛ መፍትሄ ባይሆንም "መልስ" ሆኖ ይቀርባል (ሃሊዲያናና ዶዊንግ፣ 1989a እና በርተንና ሌሎች፣ 1991)፡፡

እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎችን ለፈተና ማቅረብ የማይመከር መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይመክራሉ፡፡ ለዚህም ተማሪው ትክክል ያልሆነውን መርጦ ውጤት አገኘ ማለት ሙሉ ዕውቀት አለው የሚል ድምዳሜ ላይ አያደርስም ሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ (ግሩኖልድ፣ 2003፤ ሃሊዲያናና ዶዊንግ፣ 1989a እና በርተንና ሌሎች፣ 1991)፡፡

*መ) ባለብዙ መልስ አቀራረብ*

ይህ አቀራረብ ለአንድ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች ሁለትና ከዚያ በላይ ትክክለኛ ምላሾችን እንዲመርጡ የሚያዝ ነው (በርተንና ሌሎች፣ 1991)፡፡ ሃሊዲያናና ዶዊንግ (1989a) በዚህ ዘዴ የሚቀርቡ ጥያቄዎች አስተማማኝነታቸው ዝቅተኛ፣ የክብደት ደረጃቸውም ከፍተኛ በመሆኑና ለውጤት አመዘጋገብም ውስብስብነት ስለሚታይባቸው የማይመከሩ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የዘርፉ ምሁራን ከመልስ አስመራጭ ጥያቄ አቀራረቦች ባለአንድ መልስ ጥያቄን መጠቀም የተሻለ አስተማማኝነትና ትክክለኛነት አለው በማለት ይመክራሉ (ግሩኖልድ፣ 2003፤ ሃሊዲያናና ዶዊንግ፣ 1989a እና ርተንና ሌሎች፣ 1991)፡፡

## 2.8 የመልስ አስመራጭ ጥያቄ ብቃት ግምገማ

ማንኛውም ፈተና ፍጹምና ትክክለኛ ሊሆን አይችልም፡፡ እንደአንድ መሳሪያ ግን የትምህርቱ ዓላማ ግቡን መምታቱን ለማረጋገጥ ከሌሎች ጋር ሲወዳደር የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡ ውጤታማ የሆነ የመሳሪያ አጠቃቀምም በባለሙያው ችሎታና ዕውቀት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ባለሙያው ፈተናውን ለምን አገልግሎት እንደሚፈትን በቅድሚያ ማቀድ ይኖርበታል፡፡ ለፈተና የሚዘጋጀው የጥያቄ አይነት ዋናውን የተፈታኙን የአፈታተን ሁኔታ ጠቅላላ አዘገጃጀቱን ስለሚገልጽ አቀራረቡን መገምገም በመጀመሪያ ደረጃ የሚታሰብ ጉዳይ ነው በማለት (ብራውን፣ 1996) ይገልጻሉ፡፡

በአብዛኛው መምህራን ከፈተና አቀራረብ ይልቅ ትኩረት የሚሰጡት ለተማሪዎች ውጤት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎች ውጤት የፈተናውን አቀራረብ ጥንካሬ ይገልጻል ማለት አይደለም፡፡ በመሆኑም የፈተና አቀራረቡን በመገምገም መሻሻል የሚገባቸውን በመለየት ማሻሻል ተገቢ ነው፡፡ይህ የግምገማ ሥርዓት የፈተና አቀራረብ ግምገማ ሲባል የእያንዳንዱን ጥያቄ አዘገጃጀት በመመርመር ግልጽነት ያልጎደላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣ ለማሻሻል የሚያስችሉ የመፍትሄ ስልቶችን መወሰንና በየጊዜው በሚዘጋጁ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎችን ጥራት በማረጋገጥ ለተፈታኙ ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም የፈተና አቀራረብ ግምገማ፣ የተዘጋጀው ፈተና ምን ያህል የትምህርት ግቡ እንደተሳካና በጥያቄዎቹ የተካተቱት የትምህርት ይዘቶች ተፈታኙ በትክክል መረዳቱን ለማረጋገጥ እንደሚያስችል ማጤን ይገባል፤ (ብራውን፣ 1996) እንደገለጹት፡፡

ተማሪው በእውቀት ወይም በክሂል ዘርፍ ወደተፈለገው ግብ መድረሱን ለመለየት እንፈትነዋለን፡፡ ለዚህም ተገቢውን የመፈተኛ ዘዴ ወይም የፈተና ዓይነት ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ የፈተና አይነት ሲባል ፈተናው ተዘጋጅቶ ለተፈታኙ የሚቀርብበት የተለያየ ስልት የሚመለከት ነው (ግሮሉንድ፣ 1988)፡፡ በተመሳሳይ ብራውን (1996) እንደሚገልጹት ፈተና ትኩረት የሚያደርገው የተቀረጸውን የትምህርት ዓላማና የትምህርት ይዘት ነው፡፡ ስለሆነም የትምህርት ይዘቱን ለመፈተን የሚያስችል የፈተና ዓይነት በመለየት እንዲጣጣም ማድረግ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ሰፊ የትምህርት ይዘትን ለመሸፈን የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች ማዘጋጀት የተሻለ ነው፡፡ ሁፍስ (2003) እንደሚገልጹት የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች

መፃፍ ወይም ማዘጋጀት ቀላል መስሎ ቢታይም ተገቢና ትክክለኛ የምርጫ ጥያቄዎችን መቅረጽ ግን በጣም ከባድ በመሆኑ ልምድና ትኩረትን የሚጠይቅ ነው፡፡

የመልስ አስመራጭ ፈተና አዘገጃጀት በራሱ ውስንነቶች ያሉት ቢሆንም ሰፊ ይዘት መሸፈን ማስቻሉ፣ ለእርማት አመቺ መሆኑ፣ ተተግባሪነቱና የመሳሰሉት ጠንካራ ጎኖች ስላሉት እንደአማራጭ ሊወሰድ ይችላል (ብራውን፣ 1996)፡፡ እንደግሮንሉንድ (1988)፣ ባችማን 1990) እና ብራውን (1996) አገላለጽ በቋንቋ ፈተና የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች አቀራረብ ሲታሰብ ጥያቄዎቹን ከመሪ ጥያቄ አጻጻፍ (Writing the Steam) እና ከአማራጮች አጻጻፍ (Writing the Choices) መርሆዎች አንፃር መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

እንደምሁራኑ አገላለጽ የመሪ ጥያቄ አጻጻፍን አስመልክቶ፣ እያንዳንዱ ጥያቄ ግልፅና በቂ መረጃ የያዘ ነው? እያንዳንዱ ጥያቄ አላስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎችና የቃላት ክምችት የጸዳ ነው? መሪ ጥያቄው በአዎንታዊ አቀራረብ የተፃፈ ነው? አሉታዊ አጠያየቆች ጥቅም ላይ ከዋሉ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸዋል? ለትክክለኛው ምላሽ ጉልህ ፍንጭ የሚሰጥ በመሪ ጥያቄ ውስጥ አለ? የአጻጻፍ ስልት፣ የሰዋሰው፣ የሥርዓተ ነጥብና የሆሄያት ሁኔታና አቀማመጥ ትክክል ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መመርምር ተገቢ እንደሆነ ይመክራሉ (ግሮንሉንድ፣ 1988፤ ባችማን፣ 1990 እና ብራውን፣ 1996)፡፡

አክለውም የአማራጮች አጻጻፍን፣ አሳሳቾች የሚስቡና ተአማኒነት ያላቸው ናቸው? ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲኖረው ተደርጎ ተዘጋጅቷል? "ሁሉም መልስ ናቸው" እና "ሁለም መልስ አይደሉም" የሚል አማራጮች ጥቅም ላይ ውለዋል? የትክክለኛ መልሶች አቀማመጥ ዘፈቀዳዊና ተዘበራርቀው የተቀመጡ ናቸው? በትክክለኛው ምላሽና በአሳሳቾች መካከል በአጻጻፍ የጎላ የርዝመት ልዩነት ታይቷል? ፍጹም መለያ የሆኑ ቃላት በአሳሳቾቹ ውስጥ ተካተዋል? አማራጮቹ ከላይ ወደታች የተደረደሩ ናቸው? ከመሪ ጥያቄው ጋርስ በተመሳሳይ ገጽ ላይ ቀርበዋል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት መፈተሽ እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

### 2.8.1 የመሪ ጥያቄ አጻጻፍ (Writing the Steam)

#### 2.8.1.1 እያንዳንዱ ጥያቄ ግልፅና በቂ መረጃ የያዘ ነው?

መሪ ጥያቄው ለተማሪዎች አሻሚ እንዳይሆን በተቻለ መጠን ጠቃሚና በቂ መረጃዎችን መያዝ እንደሚገባው (ሙሊስና ማርቲን፣ 2011 እና ሂተን፣ 1988) ይመክራሉ፡፡ በተመሳሳይ ዶውን ዚማሮ (2004) እንደገለጹት በመሪ ጥያቄው መፍትሄ ወይም ምላሽ የሚያሻው ችግር ግልፅ በሆነ መልኩ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሀሊዲያና፣ ዶወኒንግና ሮድሪጌዝ (2002) መሪ ጥያቄው ዋናውን ወይም ማዕከላዊውን ሃሳብ መያዝ እንደሚገባው ይመክራሉ፡፡

#### 2.8.1.2 እያንዳንዱ ጥያቄ አላስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎችና የቃላት ክምችት የጸዳ ነው?

የማያስፈልጉ መረጃዎች በጥያቄው ውስጥ መካተት የለባቸውም፡፡ አላስፈላጊ መረጃዎች በመሪ ጥያቄው ውስጥ መካተት ሊጠየቅ የተፈለገውን ይዘት የሚሸፍን ከመሆኑም በላይ ትክክለኛውን መልስ የሚያውቁ ተማሪዎችን ሳይቀር ሊያሳሳት ይችላል፤ (በርተንና ሌሎች፣ 1991፤ ሂተን፣ 1988 እና ሙሊስና ማርቲን፣ 2011) እንደገለጹት፡፡

#### 2.8.1.3 መሪ ጥያቄው በአዎንታዊ አቀራረብ የተፃፈ ነው? አሉታዊ አጠያየቆች ጥቅም ላይ ከዋሉ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸዋል?

አሉታዊ የቃላት አጠቃቀም እንደ “ያልሆነው፣ አይደለም፣ በጥቂቱ፣ ከ…በቀር” እና የመሳሰሉትን በመሪ ጥያቄው ውስጥ በተቻለ መጠን አለመጠቀም እንደሚበጅ በመግለፅ ድርብ አሉታዊ ቃላት (በመሪ ጥያቄውና በአማራጮች) መጠቀም ተገቢ አለመሆኑን (ዶወን ዚማሮ፣ 2011፤ ሃሊዲያና፣ ዶውኒንግና ሮድሪጌዝ፣ 2002 እና ሙሊስና ማርቲን፣ 2011) አያያዝው ይመክራሉ፡፡ በአዎንታዊ መልክ የተጻፉ አማራጮች በአሉታዊ ከተገለጹት በተሻለ ጠቃሚ የሆኑ የትምህርት አላማዎችን እንደሚለኩና የአማራጮቹንም ውስብስብነት የሚቀንሱ መሆኑን ጠቅሰው ይህም የፈተናውን ትክክለኛነትና ተገቢነት እንደሚያሳድገው (ዶውን ዚማሮ፣ 2011፤ ሃሊዲያና፣ ዶውኒንግና ሮድሪጌዝ፣ 2002 እና ሙሊስና ማርቲን፣ 2011) ያስረዳሉ፡፡ ፡

ያም ሆኖ አሉታዊ ቃላት መጠቀም የግድ አስፈላጊ ከሆነ ለቃላቱ አትኩሮት በመስጠት በማተለቅ፣ ከስር በማስመር ወይም ደመቅ አድርጎ በመፃፍ ተማሪዎች በቀላሉ እንዲለዩዋቸው ማድረግ ይገባል በማለት የዘርፉ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡

### 2.8.1.4 ለትክክለኛው ምላሽ ጉልህ ፍንጭ የሚሰጥ በመሪ ጥያቄ ውስጥ አለ?

በመሪ ጥያቄው ውስጥ ያለው ቃል ወይም ሀረግ በቀጥታ መልስ ሊሆን ከሚችለው አማራጭ ጋር ከተገናኘና ፍንጭ ሰጪ የቃላት አጠቃቀም ካለ ተማሪው አሳሳቾችን ሳይመረምር በቀላሉ እንዲመልስ ያደርገዋል፡፡ ይህም በአሳሳች የቀረቡት አማራጮች ያላቸውን ፋይዳ ዝቅ ከማድረግ አልፎ የፈተናውን ትክክለኝነት ይጎዳዋል (ግሮንሉንድ፣ 1988፤ ብራውን፣ 1996 እና ሃሊዲያናና ሌሎች፣ 2011)፡፡

### 2.8.1.5 የአጻጻፍ ስልት፣ የሰዋሰው፣ የሥርዓተ ነጥብና የሆሄያት ሁኔታና አቀማመጥ ትክክል ነው?

በጥያቄ አጻጻፍ ትኩረት ከሚሰጠው ነገር አንዱ የመሪ ጥያቄውና የአማራጮቹ አቀራረብ ነው፡፡ የዘርፉ ምሁራን እንደሚስማሙበት በአማራጮች ውስጥ ተመሳሳይ የቃላት ወይም የሀረጋት ድግግሞሽን ማስወገድ ይገባል፡፡ እንደነዚህ አይነት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ የሚደጋገሙትን ቃላት ወይም ሀረጋት በመሪው ጥያቄ ውስጥ በማካተት ድግግሞሹን ማስቀረት ይቻላል፡፡ በዚህም ተማሪው በየምርጫዎቹ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ቃላትን ወይም ሀረጋትን በማንበብ የሚያጠፋውን ጊዜ በመቀነስ ሰዓቱን በአግባቡ ለመጠቀም ያስችለዋል (በርተንና ሌሎች፣ 1991፤ ክሌይ፣ 2001፤ ሂተን፣ 1990 እና ሙሊስና ማርቲን፣ 2011)፡፡

## 2.8.2 የአማራጮች አጻጻፍ (Writing the Choices)

### 2.8.2.1 አሳሳቾቹ የሚስቡና ተአማኒነት ያላቸው ናቸው?

ተአማኒነት ያላቸው አሳሳቾችን ለመቅረጽተማሪዎች ይፈጽሟቸዋል የሚባሉ ግድፈቶችን (Errors) እና የጽንሰ ሃሳብ ችግሮችን (misconceptions) መሰረት ማድረግ ይገባል፡፡ ይህ ማለት ግን ሆን ብሎ ለማሳሳት ወይም ለማታለል ይዘጋጃሉ ማለት እንዳልሆነ (ሙሊስ እና ማርቲን፣ 2011)ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ ግሮንሉንድ (1988) ተአማኒነት ያላቸው አሳሳቾች በቂ እውቀት የሌላቸውን ተማሪዎች የሚስቡ ሊሆን ይገባል፡፡ ለዚህም የተለመዱ የፅንሰ ሀሳብ መዘባትና ስህተትን መጠቀም፣ አማራጭ ምላሾችን ከአንድ ምንጭ (homogenous) መምረጥ፣ አፃፃፉ ተማሪው ሊረዳው በሚችል ቋንቋ ማቅረብና በቋንቋ ረቂቅነትና በርዝመት ተቀራራቢ ማድረግ ይገባል በማለት ይመክራሉ፡፡

በአማራጮች ቁጥር የዘርፉ ምሁራን የተለያየ ብዛት ያላቸው አሳሳቾች (ከሦስት-ሰባት) የሚጠቅሱ ቢሆንም በርካታ ምሁራን ተአማኒነት ያላቸው አሳሳቾች ለማዘጋጀት ባለአራት አማራጮችን እንደሚደግፉ ገልጸዋል፡፡ ጥናቶችን ዋቢ በማድረግም አማራጮች በበዙ ቁጥር ከትክክለኛው መልስ ጋር በጣም የተቀራረቡና በቀላሉ የማይለዩ አሳሳቾችን መቅረጽ ከባድ እንደሚሆን ገልጸው ከሦስት እስከ አራት አማራጮችን ማዘጋጀት የተሻለ እንደሆነ ይመክራሉ (ሃሊዲያና፣ ዶውኒንግና ሮድሪጌዝ፣ 2002)፡፡

### 2.8.2.2 ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲኖረው ተደርጎ ተዘጋጅቷል?

ለመልስ አስመራጭ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ በሁለት መልኩ ሊቀርብ እንደሚችል የዘርፉ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ አንደኛው አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲኖረው ታስቦ የሚዘጋጅ ሲሆን ሁለተኛው ከቀረቡት አሳሳቾች ውስጥ አንዱ ይበልጥ የተሻለ ወይም ምርጥ መልስ ሆኖ ይቀረፃል፡፡ በመሪ ጥያቄው ለቀረበው ችግር ከአንድ በላይ መልስ የሚሆኑ አማራጮች እንዳይቀርቡ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመምክር ከአንድ በላይ ትክክለኛ መልስ ያለው ጥያቄ ማቅረብ በተማሪዎች ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚኖረው በመሆኑ የፈተናውን ትክክለኝነትና አስተማማኝነት ዋጋ ያሳጣዋል በማለት (ግሮንሉንድ፣ 1988፤ ባችማን፣ 1990፤ ቡሩተንና ሌሎች (1991) እና ብራውን (1996) ይገልጻሉ፡፡

### 2.8.2.3 "ሁሉም መልስ ናቸው" እና "ሁሉም መልስ አይደሉም" የሚሉ አማራጮች ጥቅም ላይ ውለዋል?

ግሩኖልድ (2003) "ሁሉም መልስ ናቸው" የሚለውን እንደ አሳሳች ወይም ትክክለኛ ምላሽ መጠቀም ተገቢ አለመሆኑንና ይህም የሚመነጨው በቂ አማራጭ ለመፈለግ ትኩረት ከማጣት የተነሳ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በርተንና ሌሎች (1991) "ሁሉም መልስ ናቸው" የሚለውን አማራጭ ሙሉ በሙሉ መጠቀም እንደማይገባ በመግለጽ "ሁሉም መልስ

ናቸው" *ትክክለኛ መልስ* ሆኖ ሲያገለግል ተማሪዎች ከተሰጡት አማራጮች ሁለቱን ብቻ በማወቅ ባልተሟላ ግንዛቤ መልሱን ማግኘት ይችላሉ፡፡ *አሳሳች ምላሽ ሆኖ* ሲቀርብ ደግሞ አንዱ አማራጭ የተሳሳተ ምላሽ መሆኑን ተማሪዎች ካወቁ "ሁሉም መልስ ናቸው" የሚለው ምላሽ የአሳሳችነት ፋይዳ ያጣል በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

"ሁሉም መልስ አይደሉም" የሚለውን አማራጭ አጠቃቀም አስመልክቶ የዘርፉ ምሁራን የተለያዩ አመለካከቶች አሏቸው፡፡ ግሮንሉንድ (1988) እና ኢቤልና ፍሬስብ (1991) እንደሚገልጹት "ሁሉም መልስ አይደሉም" የሚለውን አማራጭ አልፎ አልፎ በጥንቃቄ መጠቀም ይቻላል ሲሉ ይመክራሉ፡፡

በአንፃሩ በርተንና ሌሎች (1991) እንደ "ሁሉም መልስ ናቸው" አማራጭ "ሁሉም መልስ አይደሉም" የሚለውን በአማራጭ ውስጥ መጠቀም እንደማይገባ ይገልፃሉ፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት መከራከሪያ "ሁሉም መልስ አይደሉም" *ትክክለኛ መልስ* ሲሆን ስሕተት የሆኑ መልሶችን ትክክል ከሆኑ መልሶች ብቻ ይለካል፡፡ "ሁሉም መልስ አይደሉም" *አሳሳች* ሆኖ ሲቀርብ ለተወሰኑ ተማሪዎች ትክክለኛ ምላሽ የመምሰል (plausible) ሁኔታ የለውም ይላሉ፡፡

እንደሂተን (1975) ገለፃ ባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ አንድ ጥያቄ በእርግጠኝነት አንድ መልስ ብቻ እንዲኖረው ማድረግ ይገባል፡፡ ትክክል ያልሆኑ አሳሳች አማራጮችም ቢያንስ በተወሰኑ ተፈታኞች የሚመረጡ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም ተፈታኙ የተወሰኑ አማራጮችን ብቻ በማወቁ ሌሎችን ባያውቃቸው እንኳን መልሱን በቀላሉ ስለሚረዳው የፈተናውን የመለካት አቅም ከፍ ለማድረግ "ሁሉም መልስ ናቸው" ወይም "ሁሉም መልስ አይደሉም" የሚለውን አመራጭ አለመጠቀም ተገቢ ነው፡፡
ክሌይ (2001) "ሁሉም መልስ ናቸው" ወይም "ሁሉም መልስ አይደሉም" የሚለውን አማራጭ አልፎ አልፎ መጠቀም እንደሚቻልና ያም ሆኖ አማራጮቹ ሲቀረፁ አሳሳች ከሚሆኑ ይልቅ ትክክለኛ መልስ ቢሆኑ እንደሚሻል ያስገነዝባሉ፡፡

### 2.8.2.4 በትክክለኛው ምላሽና በአሳሳቾች መካከል በአፃፃፍ የጎላ የርዝመት ልዩነት ታይቷል?

በመልስ አስመራጭ ጥያቄ ዝግጅት ወቅት ከሚያጋጥሙት ተደጋጋሚ ስህተቶች ትክክለኛው መልስ ከአሳሳቾች ረዝሞ መገኘት መሆኑን በመጠቆም ይህም ችግር ተማሪዎች በቀላሉ የአማራጩን ርዝመት በመጠቀም ትክክለኛውን መልስ ሊገምቱ ይችላሉ፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ የአማራጮቹ ርዝመት ተቀራራቢ መሆን እንደሚገባው የዘርፉ ምሁራን ይገልፃሉ (ክሌይ፣ 2001፤ በርተንና ሌሎች፣ 1991 እና ሂተን፣ 1988)፡፡ በተመሳሳይ ዳንኤል (2006) እንደሚገልጹት የምርጫ ጥያቄ መልስ የመርዘም አዝማሚያ የሚኖረው መልሱ ትክክል ስለመሆኑ አጠንክሮ ስለሚታሰብ ነው፡፡ አያይዘውም በፈተና ብልህ ለሆኑ ተፈታኞች ሁኔታው ለትክክለኛው መልስ ፈንጭ ሊሆናቸው እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡

### 2.8.2.5 ፍጹም መለያ የሆኑ ቃላት በአሳሳቾቹ ውስጥ ተካተዋል?

ፈፅሞ፣ ሁሉም፣ ምንም፣ ሁልጊዜ፣ ብቻ እና የመሳሰሉት ፍጹም መለያ የሆኑ ቃላት በአብዛኛው ሀሳቡ ሀሰት እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ እንደነዚህ አይነት ቃላት በአሳሳች አማራጮች ውስጥ መካተት ተማሪዎች በቀላሉ በመለየት እንዲያስወግዱዋቸው እድል ይሰጣል፡፡ ስለሆነም በመሪ ጥያቄው ለቀረበው ችግር ተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ በቀላሉና በግልፅ ለመለየት ስለሚረዳቸው ባልተሟላ እውቀት በግምት ብቻ መልሱን ሊያገኑ ይችላሉ (ክሌይ፣ 2001 እና በርተንና ሌሎች፣ 1991)፡፡ በተመሳሳይ ፍጹም መለያ ቃላትን የያዙ አማራጮች መልሱን ምንም የማያውቁ ተፈታኞች አማራጮቹን በማስወገድ በግምት ትክክለኛውን መልስ የማግኘት እድላቸውን ከፍ ያደርጋል (ሁፍስ፣ 2003፤ ታነር፣ 2003)

### 2.8.2.6 አማራጮቹ ከላይ ወደታች የተደረደሩ ናቸው? ከመሪው ጥያቄ ጋርስ በተመሳሳይ ገጽ ላይ ቀርበዋል?

በርካታ የዘርፉ ምሁራን እንደሚስማሙበት የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አማራጮች ከላይ ወደታች (vertically) እንዲጻፉ ይመክራሉ፡፡ በተጨማሪም መሪ ጥያቄውና ሁሉም አማራጮች በተመሳሳይ ገጽ ላይ መቅረብ እንደሚገባቸው በመምከር ጥያቄውና አማራጮች በተለያየ ገጽ ላይ ቢጻፉ ተማሪዎቹ ከአንዱ ገጽ ወደሌላው ገጽ ለማንበብ ሲያገላብጡ ጊዜያቸውን ያባክንባቸዋል (ሃሊዲያና፣ ዶውኒንግና ሮድሪጌዝ፣ 2002፤ ዶውን ዚማሮ፣ 2004፤ ብሬይን ቶምሊንሰን፣ 2005 እና በርተንና ሌሎች፣ 1991)፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፡- የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የምርምሩ ስልት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና ጥያቄዎች አቀራረብ ትንተና /item format analysis/ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ ሙሉ በሙሉ መልስ አስመራጭ በመሆናቸው ከ2005-2007 ዓ.ም ድረስ ያሉት የሦስት ዓመታት ፈተናዎች መሪ ጥያቄና አማራጮች ከመልስ አስመራጭ ጥያቄ መርሆች አንፃር መዘጋጀታቸውን ይገመግማል፡፡ ጥናቱ መሰረት ያደረገው አጠናን በዋናነት ዓይነታዊ ምርምር /Qualitative/ ዘዴን በመጠቀም የተሰበሰቡትን መረጃዎች መገምገም ሲሆን ከመርሁ አንጻር ክፍተት የታየባቸውን ጥያቄዎች ብዛት በአሀዝና በመቶኛ ለማስላት እንዲቻል መጠናዊ ምርምር ዘዴም ጥቅም ውሏል፡፡ የጥናቱ ውጤትም የሚቀርበው ገለጻዊ መንገድን ተከትሎ ነው፡፡ ይህ የጥናት ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም ተመራማሪው እያንዳንዱን ጥያቄ ከመርሆቹ አንፃር በመፈተሽ በጥናቱ ያገኘውን ውጤት፣ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ ለማቅረብ ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ ነው፡፡

የጥናቱ ትኩረትም ጥያቄዎቹ ከመልስ አስመራጭ ፈተና አዘገጃጀት መርሆች አንፃር መዘጋጀታቸውን መመርመር ሲሆን ለዚህም የሃሊድያና፣ ዶውኒንግ እና ሮድሩጌዝ (2002)፣ የግሮንሉንድ (1988) እና ብራውን (1996) የፈተና አዘገጃጀት መርሆች ከጥናቱ አላማ አንጻር እንዲስማሙ በማድረግ በመገምገሚያ መስፈርትነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ2005-2007 ዓ.ም ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበውን ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄ አቀራረብ (Item format analysis) መተንተን ነው፡፡ ስለሆነም ለጥናቱ የሚያስፈልጉት መረጃዎች የሚሰበሰቡት ሙሉ በሙሉ በሦስቱ ዓመታት ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄ ወረቀቶች ላይ ይሆናል፡፡ የእያንዳንዱ አመት ፈተና ስድሳ ስድሳ ጥያቄዎችን የያዘ በመሆኑ በሦስቱ አመታት ፈተናዎች አንድ መቶ ሰማኒያ ጥያቄዎች በጥናቱ ተፈትሸዋል፡፡ ሰነዱ ከወሳኝ ንሞና (non-probability) ዘዴ የዒላማ ንሞና አወሳሰድን (purposive) በመጠቀም ለመረጃ

ምንጭነት ተወስዷል፡፡ ሰነዱ እንደመረጃ ምንጭ ከወሳኝ ንሞና በዒላማ ንሞና የተመረጠበት ምክንያት ለጥናቱ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

## 3.3 መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

ጥናቱ ሙሉ በሙሉ የሚያተኩረው በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ጥያቄዎች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መሰረት ያደረገው የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ይህ ጥናት ዋነኛ ትኩረቱ ለሆነው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ2005-2007 ዓ.ም ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ለቀረበው ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ለጥያቄ አቀራረብ ትንተና ተገቢ መረጃ ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ስልት

በጥናቱ ተተኳሪ የሆነው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የሦስት ተከታታይ ዓመታት (2005-2007) የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና የጥያቄ አቀራረብ ትንተና (item format analysis) የሚከናወነው የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አዘገጃጀት መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡ በሃሊድያና፣ዶውኒንግ እና ሮድሩጌዝ (2002)፣ በግሮንሉንድ (1988) እና በብራውን (1996) የፈተና አዘገጃጀት መርሆች ከተጠቀሱት ዝርዝር መርሆዎች ይህ ጥናት ሊመልሳቸው ካነሳቸው መሪ ጥያቄዎች አንጻር በሁለት ክፍሎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በዚህም መሰረት በመሪ ጥያቄ አጻጻፍ (Writing the Steam) ስር አምስት መርሆች፣ በአማራጮች አጻጻፍ (Writing the Choices) ስር ስድስት መርሆች በመጠቀም የጥያቄዎቹ አቀራረብ የሚተነተን ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት

## 4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ከ2005-2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው ለ8ኛ ክፍል የቀረቡትን የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና የጥያቄ አቀራረብ /item format / ከምርጫ ፈተና አዘገጃጀት መርሆዎች አንጻር መዘጋጀታቸውን መገምገም ነው፡፡ ግምገማውም በሁለት አቢይ ክፍሎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እነዚህም *የመሪ ጥያቄ አጻጻፍ (Writing the Steam)* እና *የአማራጮች አጻጻፍ (Writing the Choices)* ናቸው፡፡ የሦስቱ አመታት ፈተናዎችም በእነዚህ አቢይ ክፍሎችና በሥራቸው በሚቀርቡ ዝርዝር መስፈርቶች ላይ በመመስረት ይፈተሻሉ፡፡

እነዚህን መርሆዎች መሰረት በማድረግ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና መሪ ጥያቄዎች ከጥያቄ አቀራረብ አንፃር ምን ያህል መርሆዎቹን የጠበቁ ናቸው? እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄዎቹ አማራጮች፣ የአማራጮች አቀራረብን ምን ያህል ያሟላሉ? የሚሉትን የጥናቱን ቁልፍ ጥያቄዎች ለመመለስ በዚህ ምዕራፍ ከ2005-2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ምን እንደሚመስሉ ተፈትሿል፡፡

በእነዚህ ሦስት ተከታታይ ዓመታት ለየአመቱ 60 ጥያቄዎች የተዘጋጁ ሲሆን በጠቅላላው 180 ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ፈተናዎቹ በመልስ አስመራጭ ጥያቄ በመዘጋጀታቸው ሁሉም ጥያቄዎች ከመርሆዎቹ አንጻር ተፈትሸው የጥናቱ ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 4.1.1 መሪ ጥያቄ አጻጻፍ (Writing the Stem)

በዚህ መርህ ስር አምስት ንኡሳን መርሆዎችን መሰረት በማድረግ መሪ ጥያቄው ይፈተሻል፡፡ እነዚህም የጥያቄ አቀራረብ ግልጽነት፣ ጥያቄው ከማያስፈልጉ መረጃዎች የጸዳ ስለመሆኑ፣ ጥያቄው በአዎንታዊ አቀራረብ ስለመዘጋጀቱ፣ አሉታዊ አቀራረቦች ጥቅም ላይ ውለው ከሆነ ተገቢው ትኩረት ስለመሰጠቱ እና የጥያቄው አቀራረብ ለአማራጭ መልሶች

ፍንጭ ሰጪ መሆን አለመሆኑ እንዲሁም የአጻጻፍ ስልት፣ የሰዋሰው፣ የሥርዓተ ነጥብና የሆሄያት ሁኔታና አቀማመጥ ናቸው፡፡

#### 4.1.1.1 እያንዳንዱ ጥያቄ ግልፅና በቂ መረጃ የያዘ ነው?

ከዚህ መርህ አንጻር በሦስት ዓመታት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ምን እንደሚመስሉ ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት የሚከተሉት ጉድለቶች ታይቶባቸዋል፡፡

<u>ከ2005 ዓ.ም ፈተና፣</u>

ጥያቄ 9. ከቀረበው ምንባብ ለወጡት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ከሚከተሉት የንባብ አይነቶች የትኛውን መጠቀም ግድ ይላል?

A. የአሰሳ ንባብ
C. የገረፍ ገረፍ ንባብ
B. የፍጥነት ንባብ
D. የዝግታ ንባብ

ጥያቄው ከምንባቡ የወጡትን 11 ጥያቄዎች በአንድ የንባብ ስልት ብቻ መመለስ እንደሚቻል አድርጎ ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጂ አንቀጽ ተጠቅሶ የቀረቡ ጥያቄዎችንና ምንም ጥቆማ ሳይሰጥ የቀረቡ ጥያቄዎችን በተመሳሳይ የንባብ ስልት አንብቦ መመለስ አይቻልም፡፡ ለምሳሌ፣ ጥያቄ 7 ን ለመመለስ ምንባቡን ማንበብ ይጠይቃል፡፡ ጥያቄ 8 ን ለመመለስ ደግሞ የ3ኛውን አንቀጽ መጀመሪያ ማየት በቂ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪው ጥያቄዎችን ለመመለስ የተለያዩ ዘዴዎችን ለመጠቀም ይገደዳል፡፡ ስለዚህ ጥያቄው ግልጽነት የሚጎድለው ሲሆን በቂ መረጃም የያዘ አይደለም፡፡

<u>ከ2006 ዓ.ም ፈተና፣</u>

ጥያቄ. 1 የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ የሚጎድለው የሥርዐተ ነጥብ አይነት የቱ ነው?

A. ድርብ ሰረዝ
C. አራት ነጥብ
B. ነጠላ ሰረዝ
D. ትእምርተ አንክሮ

በምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ ከአንድ በላይ ሥርአተ ነጥቦች ይጎድላል፡፡ ለአብነት “ ቆይ ደግሞ እንገናኛለን” ለሚለው የዛቻ አገላለጽ ትእምርተ አንክሮ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም “... እየተጎማለለ እየፎከረ... እየዛተ እያስፈራራ ስፍራውን ለጥቢ ፀሐይ እየለቀቀ...”

በሚሉት መዘርዝሮች መካከል የነጠላ ሰረዝ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በጥያቄው ውስጥ ለመጠየቅ የተፈለገው የት ቦታ ላይ የጎደለውን ሥርዓተ ነጥብ እንደሆነ በግልጽና በበቂ መረጃ ተዋቅሮ አልቀረበም፡፡

በዚሁ በ2006 ዓ.ም በቀረበው ፈተና ጥያቄ 2 እና 5 የተማሪዎችን ጊዜ ሊቆጥብ የሚችል ጥያቄ አለመቅረቡን ማስተዋል ይቻላል፡፡

ጥያቄ 2. "ጥቢ" ለሚለው ቃል የሚስማማው ፍቺ የትኛው ነው?

A. በጋ ውጭ ግንቦት C. ክረምት ውጪ መስከረም

B. በልግ ውጪ ሰኔ D. ፀደይ ውጭ ሕዳር

ጥያቄ 5. በምንባቡ ውስጥ በትልቁ ሉል የተመሰለችው ምንድናት?

A. ጨረቃ C. አዲስ አበባ

B. ፀሐይ D. መሬት

በመሪ ጥያቄው ውስጥ የሚገኙት ጥቢ እና ሉል የሚሉትን ቁልፍ ቃላት በምንባቡ ውስጥ የሚገኙበትን አንቀፅ ባለመጠቆሙ ወይም በምንባቡ ውስጥ ከስር በማስመር ወይም በማድመቅ በቀላሉ እንዲለዩ ባለመደረጉ ተማሪዎች ቃላቱን ፍለጋ እንዲባዝኑ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጠው አንድ ደቂቃ ጊዜ አንጻር (በገፅ 1 ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው) ቁልፍ ቃላቱን በተለያየ (አንቀጽ በመጠቆም ወይም በምንባቡ ውስጥ ለየት ባለ አጻጻፍ በማመልካት) መንገድ በመጠቆም ጥያቄውን የበለጠ ግልጽ ማድረግ ይቻላል፡፡

<u>ከ2007 ዓ.ም ፈተና</u>

ጥያቄ 28. "ባለችው መጠቀም ጥሩ ነው" የሚለውን በምሣሌያው አነጋገር ለመግለጽ ከሚከተሉት የትኛው ተስማሚ ነው?

A. ከበላ ብላ ከሰው አትጣላ፡፡ C. ማምሻም ዕድሜ ነው፡፡

B. ምጡን እርሺው ልጁን አንሺው፡፡ D. ሞኝ አሞራ ያባቱን ዋሻ ይጠየፋል፡፡

ለተማሪዎች የሚቀርብ ጥያቄ ግልጽ፣ በቂ መረጃ የሚሰጥና አሻሚነት የማይታይበት መሆን ይገባዋል፡፡ በዚህ ጥያቄ ውስጥ ትክክለኛው ምላሽ የሚወሰነው በመጀመሪያ ላይ የሚገኘው ቃል ሲጠብቅና ሲላላ በሚሰጠው ትርጉም ነው፡፡ የጥያቄው ዓላማ ግን ይኸ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች አጥብቆ በማንበብና ባለማንበብ ብቻ መልሱን እያወቁት ሊሳሳቱ ስለሚችሉ የጥያቄውን ግልፅነት ይጎዳዋል፡፡

በአንድ መሪ ጥያቄ ውስጥ የሚቀርበው ችግር በግልጽ የተጻፈና ትኩረቱም በአንድ በተወሰነ ነገር ላይ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ በግልጽ የተጻፈ ጥያቄ ተፈታኙ ጥያቄውን በአጭር ጊዜው ውስጥ እንዲረዳ ስለሚረዳው መልሱን ለመመለስ የሚፈጀውን ጊዜ በግባቡ እንዲጠቀም ይረዳዋል (ግሮንሉንድ፣ 1988)፡፡ ከዚህ አንጻር በሦስቱ ዓመታት ከቀረቡት ፈተናዎች ውስጥ ከላይ የተጠቀሱት 6 ጥያቄዎች ከጥያቄ ግልፅነትና በቂ መረጃ ከመያዘ ጋር ክፍተት ታይቶባቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በተማሪው ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳረፉም ባሻገር የፈተናውን አስተማማኝነት ይጎዳዋል፡፡

### 4.1.1.2 እያንዳንዱ ጥያቄ አላስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎችና የቃላት ክምችት የጸዳ ነው?

የሦስቱ አመታት ፈተናዎች ከዚህ መርህ አንጻር ሲፈተሹ የጎላ ችግር ያልታየባቸው ቢሆንም በ2005 ዓ.ም ከቀረበው ፈተና ጥያቄ 10 ላይ የሚከተለው እንደክፍተት የሚታይ ነው፡፡

ጥያቄ 10. በምንባቡ ሐሳብ መሰረት ለአዲስ አበባ ሰፈሮች ስያሜ መገኘት የቀረቡት ሐሣቦች ምን ያህል እንደሆኑ የሚገልፀውን አማራጭ የያዘው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

መሪ ጥያቄውን "...የቀረቡት ሐሣቦች ምን ያህል ናቸው?" ብሎ ማቅረብ ሲቻል "...የቀረቡት ሐሣቦች ምን ያህል እንደሆኑ የሚገልፀውን አማራጭ የያዘው ከሚከተሉት የትኛው ነው?" በማለት የቀረበበት መንገድ ለአላስፈላጊ የቃላት ክምችት እንደዳረገው መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.1.1.3 መሪ ጥያቄው በአዎንታዊ አቀራረብ የተፃፈ ነው? አሉታዊ አጠያየቆች ጥቅም ላይ ከዋሉ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸዋል?

ከዚህ አንጻር በ2005 ዓ.ም እና በ2006 ዓ.ም የቀረቡት ፈተናዎች ከአሉታዊ አጠያየቅ የጸዱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በ2007 ዓ.ም ከቀረበው ፈተና በተራ ቁጥር 27 እና 42 ያሉት ጥያቄዎች በአሉታዊ አገላለጽ የተጠየቁ ሲሆን አሉታዊው አገላለጹ ከሌሎቹ አገላለፆች በቀላሉ በተማሪዎች ተለይቶ እንዲታወቅና አትኩሮት እንዲያገኝ በጉልህ አፃፃፍ ደምቆ ባለመጻፉ ከመርሁ አንጻር ጉድለት ታይቶበታል፡፡የሚከተለውን ምሳሌ ማየት ይቻላል፡፡

ጥያቄ 42፣ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ከሌሎች ጋር በፍቺ የማይመሳሰለው ቃል የትኛው ነው?

በዚህ ጥያቄ ውስጥ "የማይመሳሰለው" ሚለው አሉታዊ ቃል በተለየ ቅርጽ ሊቀርብ ይገባው ነበር፡፡ በዚህም አሉታዊውን አገላለጽ በቀላሉ ባለመለየታቸው ብቻ በተማሪዎች ውጤት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፍ ሲሆን የፈተናውን አስተማማኝነትም ይጎዳዋል፡፡

### 4.1.1.4 ለትክክለኛው ምላሽ ጉልህ ፍንጭ የሚሰጥ በመሪ ጥያቄ ውስጥ አለ?

ከዚህ መርህ አንጻር የሦስቱ አመታት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥያቄዎች ተገምግመው በ2006 እና በ2007 በተዘጋጁት ጥያቄዎች የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡፡

<u>በ2006 ዓ.ም ከተዘጋጀው ፈተና፣</u>

ጥያቄ 16. "በቃለ መጠይቅ አዘገጃጀት ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ቅድሚያ የሚሰጠው የትኛው ነው?"

A. ቃለመጠየቅ ከሚቀርብለት ሰው ጋር መተዋወቅ
B. ለተጠያቂው ስለቃለመጠይቁ ማስረዳት
C. ቃለመጠይቅ ከሚቀርብለት ሰው ጋር ቀጠሮ መያዝ
D. ለተጠያቂው የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ማዘጋጀት

በመሪ ጥያቄው ውስጥ "...አዘገጃጀት..." የሚለውን ቃል በምርጫ D ውስጥ ከሚገኘው "...ማዘጋጀት" ከሚለው ጋር በማዛመድ ትክክለኛውን መልስ ለመመለስ ዕድል ይሰጣል፡፡

ይህም በመሪ ጥያቄ ውስጥ የሚገኘው ቃል በፍንጭ ሰጪነት የሚያገለግል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ጥያቄ 34. "የጎዳና ተዳዳሪዎች የተሟላ የዕለት ጉርስ ስለማያገኙ አቅመ ደካሞች ይሆናሉ፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ውጤት ሆኖ የተገለጸው ምንድነው?

A. አቅም ማግኘት C. አቅመ ደካማ መሆን

B. የዕለት ጉርስ ማጣት D. በአቅም ማጣት መሞት

በመሪ ጥያቄው ውስጥ "...አቅመ ደካሞች ይሆናሉ ..." የሚለው ሐረግ በምርጫ C ውስጥ ለሚገኘው "...አቅመ ደካማ መሆን" ለሚለው በቂ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎችም ምንም ሳይመራመሩ ጥያቄውን መመለስ ይችላሉ፡፡

ለ2007 ዓ.ም ከቀረቡት ጥያቄዎች፣

ዓለሙን ጠፍጥፌው ቂጣ ቢጋገርሁት
ውሃውን ንጨ ቅቤ ----------------------፡፡
ባወጣሁት ቅቤ ቂጣዬን አርሼ.....

የሚቀጥለው ጥያቄ ከላይ ተቀንጭቦ በተወሰደው ግጥም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ጥያቄ 60. በሁለተኛው ስንኝ በተተወው ባዶ ቦታ ላይ ቢገባ የግጥሙን ሐሳብና ምጣኔ የተሟላ የሚያደርገው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

A. ባወጣሁት C. ጠጣሁት

B. በተቀባሁት D. በነካሁት

ይህን ጥያቄ ለመመለስ ተማሪዎች ምንም መመራመር ሳያስፈልጋቸው እዚያው በሦስተኛው ስንኝ መነሻ ሐረግ ላይ ትክክለኛውን መልስ ያገኙታል፡፡ በሌላ በኩል ምርጫ C እና D በቂ የሆነ የአሳሳችነት ሚና ስለማይኖራቸው ጥያቄው የተማሪዎችን ችሎታ የመለካት አቅሙን ያጎድለዋል፡፡

በእነዚህ ጥያቄዎች የታዩት ፍንጭ ሰጪዎች የጥያቄውን መልስ ከመጠቆም ባሻገር የፈተናውን ትክክለኛነትና ይጎዱታል፡፡

### 4.1.1.5 የአጻጻፍ ስልት፣ የሰዋሰው፣ የሥርዓተ ነጥብና የሆሄያት ሁኔታና አቀማመጥ ትክክል ነው?

በግምገማው በታዩት ፈተናዎች ውስጥ የጥያቄዎች አጻጻፍ ላይ በመሪ ጥያቄው ተካተው ቢቀርቡ በአማራጮች የታየውን የቃላትና የሐረጋት መደጋገም ማስቀረት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ከ 2005 ዓ.ም ፈተና ጥያቄ 7 "አዲስ አበባ… "፣ ከ 2006 ዓ.ም ፈተና ጥያቄ 17 "ሁለቱም… "፣ ከ 2007 ዓ.ም ፈተና ጥያቄ 2 "… ይከበራል ማለት ነው" እና ጥያቄ 59 "ምኞት… " የሚሉት በአራቱም አማራጮች በተመሳሳይ ቅርጽ መደጋገማቸው መጠነኛ ክፍተት ታይቶበታል፡፡ በሌላ በኩል በሦስቱም አመታት የአርትኦት ችግር ታይቷል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን ማየት ይቻላል፡፡

| ዓ.ም | ስህተት የታየበት ገጽ | ስህተት | ተስተካክሎ ቢጻፍ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 2005 | 5 | አንጠልጥሎ | አንጠልጥሎ | በመሪ ጥያቄ 15 ውስጥ |
| | 6 | ጉዳይ | ጉዳት | በመሪ ጥያቄ 17 ውስጥ |
| | 9 | ፀሐፊና ፀሐፍት<br>ኑግና ሰሊጥ | ፀሐፊ እና ፀሐፍት<br>ኑግ እና ሰሊጥ | ለጥያቄ 30 ከሌሎች አማራጮች አንጻር የአጻጻፍ ወጥነት ያለመኖር |
| | 15 | መስማሚያህ | መስሚያህ | በጥያቄ 55 ምርጫ C |
| | 16 | አራሁ ሁለት | አሥራ ሁለት | በጥያቄ 60 ምርጫ C |
| 2006 | 1 | ኢያለ፣ የሚደለቁ | እያለ፣ የሚደልቁ | በምንባብ ውስጥ |
| | 3 | የእግኛና | የእግረኛና | በጥያቄ 10 ምርጫ A |
| | 11 | አራት ነጥብ/ | አራት ነጥብ፣ | በጥያቄ 43 ምርጫ D |
| | 12 | ከሚከተሉት እንደሄደት | የሚከተሉት እንደሄደች | በመሪ ጥያቄ 45 |
| | 13 | አንቀፍ | አንቀጽ | በመሪ ጥያቄ 49 እና 50 |
| | 15 | የተሠረቱ | የተመሠረቱ | በክፍል አምስት መመሪያ ውስጥ |
| | 16 | ከሚነሳቸው | ከሚያነሳቸው | በመሪ ጥያቄ 60 |
| 2007 | 1 | ወላችሁ | ዋላችሁ | በምንባብ ውስጥ |
| | 2 | አጀንዳ | አሸንዳ | በምንባብ ውስጥ |
| | 11 | እማባካችሁ | እባካችሁ | በመሪ ጥያቄ 46 ውስጥ |

ከላይ ለአብነት የቀረቡት መረጃዎች በቂ የሆነ የአርትኦት ሥራ መሠራት እንደነበረበት ይጠቁማሉ፡፡

## 4.1.2 አማራጮች አጻጻፍ (Writing the Choices)

ከዚህ መርህ አንጻር አማራጮችን ለመፈተሽ ስድስት ንኡሳን መርሆዎች መሰረት ተደርገዋል፡፡ እነዚህም የአሳሳቾች ሳቢ መሆን፣ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ ስለመያዙ፣ "ሁሉም መልስ ናቸው" እና "ሁለም መልስ አይደሉም" የሚሉ አማራጮች አጠቃቀም፣ በትክክለኛው ምላሽና በአሳሳቾች መካከል በአጻጻፍ የጎላ የርዝመት ልዩነት መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ፣ ፍጹም መለያ የሆኑ ቃላት በአሳሳቾቹ ውስጥ ስለመካተታቸው መፈተሽ እና አማራጮቹ ከላይ ወደታች የተደረደሩ ስለመሆናቸው እንዲሁም ከመሪ ጥያቄው ጋር በተመሳሳይ ገጽ ስለመቅረባቸው ናቸው፡፡

### 4.1.2.1 አሳሳቾች የሚስቡና ተአማኒነት ያላቸው ናቸው?

ከዚህ መርህ አንጻር በሦስቱ አመታት (ከ2005-2007 ዓ.ም) የተፈተሹት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የተወሰኑ ክፍተቶች ታይተውባቸዋል፡፡

ከ2005 ዓ.ም ፈተና፣

ጥያቄ 30. ከ "ዕፅ እና ዕፅዋት" ጋር በቅርፅ የሚመሳሰለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ተክል እና ቡቃያ
B. ፀሐፊና ፀሐፍት
C. ኑግ እና ሰሊጥ
D. አካላት እና አባላት

አማራጭ A፣ C እና D ከጥያቄው ጋር ምንም አይነት የቅርፅ መመሳሰል የላቸውም፡፡ በጥያቄው ውስጥ የቀረበው መነሻ ሀሳብ ከአንድ ቃል የተመሰረቱ ነጠላና ብዙ ቁጥር ቅርጽ ያለው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ትክክለኛ መልስ ከያዘው አማራጭ B በቀር ሁሉም አሳሳቾች ለትክክለኛው መልስ የቀረበ የማሳሳት አቅም የላቸውም፡፡

ጥያቄ 31. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በቃላት አመሠራረት አብረው የሚሄዱ ጥንዶችን የያዘው የትኛው አማራጭ ነው?

A. በላ፣ ብልሃት
B. ነቀለ፣ ውልቃት
C. ቀጠፈ፣ ቅጥፈት
D. ቀወጠ፣ ቅብጠት

በአማራጭ B እና D የቀረቡት ጥንድ ቃላት የተለያዩ በመሆናቸው አብሮ የሚሄድ የቃላት አመሠራረት እንዲኖራቸው የሚያስችል ምንም ግንኙነት የላቸውም፡፡ በዚህም የተነሳ የአሳሳችነት ሚናቸውን መወጣት ይሳናቸዋል፡፡ በመሆኑም በቀላሉ ከመልስ ምርጫ ውጪ በመሆን የአማራጮችን ቁጥር ከአራት ወደሁለት ዝቅ እንዲል ያደርጉታል፡፡ የጥያቄውንም የመለካት አቅም ይጎዱታል፡፡

ከ2006 ዓ.ም ፈተና፣

ጥያቄ 9. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት የጀንበር ማሽቆልቆል ምንን ያመለክታል?

A. ቀኑ መዳመኑን

B. ቀኑ መጨለሙን

C. ቀኑ ተስያት መሆኑን

D. ቀኑ መምሸቱን

በአሳሳችነት የቀረቡት A እና C ከጀንበር ማሽቆልቆል ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፡፡ ስለሆነም የአሳሳችነት ሚናቸውን በአግባቡ መወጣት ስለማይችሉ የተአማኒነት ጉድለት ታይቶባቸዋል፡፡

ጥያቄ 15. ውይይት ሲጀመር ተወያዮች ጉዳዩን አስቀድመው እንዲያስቡበት አወያዩ በቅድሚያ የሚያደርገው ምንድነው?

A. የውይይቱን ተሳታፊዎች መለየት

B. የውይይቱን ውሳኔ ግልጽ ማድረግ

C. የውይይቱን አጀንዳ ማስተዋወቅ

D. ውይይቱን በሥነ-ሥርዓት መምራት

“ውይይት ሲጀመር…” የሚለውን በማየት ብቻ ተማሪዎች ትኩረታቸውን ከምርጫ A፣ B እና D ላይ ያነሳሉ፡፡ ስለዚህም መልሱን Cን ብቻ ይመርጣሉ፡፡ ይህም ለአሳሳችነት የቀረቡት A፣ B እና D ተገቢ ባለመሆናቸው የጥያቄውን የመለካት አቅም ይጎዱታል፡፡

ጥያቄ 46. "አንድ ዛፍ አለ፤ አሥራ ሁለት ቅርንጫፎች አሉት፤ እያንዳንዱ ቅርንጫፍ ሰላሣ ቅጠሎች አሉት፡፡" ለሚለው እንቆቅልሽ መልስ የሚሆነው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

A. ሰው፣ የዘር ሐረግ፣ ትውልድ
B. ዓመት፣ ወራት፣ ቀናት
C. ሀገር፣ ብሔረሰቦች፣ ሰዎች
D. መንግስት፣ ክፍለ ጦር፣ ወታደር

ለአሳሳችነት ከቀረቡት ሦስት አሳሳቾች መካከል (A፣ C እና D) አንዳቸውም ለእንቆቅልሹ ቅርብ አይደሉም፡፡ ለመልስ የቀረቡ ባለመሆናቸው የአሳሳችነት ሚናቸውን አነስተኛ ያደርገዋል፡፡

ጥያቄ 51. "ማን ያርዳ--------፣ ማን ይናገር-----------" የሚለውን ያልተሟላ ምሣሌያዊ አነጋገር በቅደም ተከተል ማሟላት የሚችለው የትኛው ነው?

A. የቀበረ፣ የነበረ
B. የነበረ፣ የቀበረ
C. የወረረ፣ የፈጠረ
D. የወገረ፣ የበረረ

ለጥያቄው ከቀረቡት አማራጮች መካከል C እና D ትኩረት የመሳብ ሀይላቸው ደካማ ነው፡፡ ምክንያቱም ምርጫ A እና B የቀረቡበት መንገድ ወደመልሱ በጣም የቀረቡ መሆናቸውን ለመገመት ዕድል የሚሰጡ በመሆናቸው ምርጫ C እና Dን በቀላሉ ከትኩረት ውጪ ያደርጉዋቸዋል፡፡ በዚህም የትክክለኛ መልስ እና የአሳሳቾች ተቀራራቢነት ጥያቄ ውስጥ ስለሚከተው ተአማኒነት ያሳጣቸዋል፡፡

<u>ከ2007 ዓ.ም ፈተና፣</u>

ጥያቄ 14. "ያልጠረጠረ ተመነጠረ" በሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር መንስኤ የሆነው ድርጊት የትኛው ነው?

A. አለመጠርጠር
B. መመንጠር
C. መጠርጠር
D. ጥርጣሬ

በምርጫ C እና D መካከል የቅርጽ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር ከጥያቄው አንጻር የሚፈጥሩት ልዩነት የለም፡፡ ተመሳሳይ ትርጉም ስላላቸውም እንደትክክለኛ መልስ እንዳይወሰዱ ያደርጋል፡፡ በሌላ በኩል ምርጫ A፣ C እና D በጥርጣሬ ዙሪያ ያጠነጠኑ

ሲሆን ምርጫ B ብቻ መመንጠር በሚል ቀርቧል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ጥያቄውን በመመርመር ከመመለስ ይልቅ C እና D ተመሳሰይ በመሆናቸው መልስ ሊሆኑ እንደማይችሉና B ደግሞ ለብቻው ለየት ብሎ መቅረቡን በማየት ትክክለኛውን መልስ በቀላሉ ሊያገኙት ይችላሉ፡፡ ይህም ትክክለኛው መልስና አሳሳቾቹ ተቀራራቢ ትኩረት እንዲስቡ ሆነው አለመቀረጻቸውን ያሳያል፡፡

ጥያቄ 15. "እዩኝ እዩኝ ማለት ደብቁኝ ደብቁኝ ማለትን ያስከትላል" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ለድርጊቱ ውጤት የሆነው የቱ ነው?

A. እዩኝ ደብቁኝ
B. እዩኝ እዩኝ
C. አትዩኝ አትደበቁኝ
D. ደብቁኝ ደብቁኝ

ምረጫ A እና C በውስጣቸው ተቃራኒ ሀሳብ ይዘው በመቅረባቸው በቀላሉ ከተማሪዎች ትኩረት ውጪ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ የአሳሳችነት ሚና ስለማይኖራቸው ተአማኒነት ይጎላቸዋል፡፡

ጥያቄ 17. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በሥርዓት መመራትን የግድ የሚል የትኛው ነው?

A. ጭውውት
B. ክርክር
C. ግልግል
D. ግርግር

ምርጫ C እና D በሥርዓት ከመመራት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፡፡ በመሆኑም ምንም ዝግጅት ያላደረገ ተማሪ እንኳ ሳይቀር ሁለቱን አሳሳቾች በማስወገድ ትክክለኛ መልስ የማግኘት ዕድሉን ያሰፋል፡፡ ለዚህም ምክንያት የሚሆነው የሁለቱ አሳሳቾች ደካማ አቀራረብ ነው፡፡

ለእነዚህ ጥያቄዎች የቀረቡት አሳሳቾች ተገቢነትና ተአማኒነት ጉድለት እንደታየባቸው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ እነዚህ ጉድለቶች ተማሪዎችን በአግባቡ ለመመዘን ያላቸውን ፋይዳም ጥያቄ ውስጥ እንደሚያስገባው ከቀረቡት አስረጂዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለአሳሳችነት የቀረቡት አማራጮቹ ተገቢ ባለመሆናቸውም የጥያቄውን ትክክለኛነት ይጎዳዋል፡፡

#### 4.1.2.2 ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲኖረው ተደርጎ ተዘጋጅቷል?

አንድ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ወይም ከሁሉ የተሻለ መልስ እንዲኖረው ከመዘጋጀት አንጻር በ2005 እና በ2006 ዓ.ም በተዘጋጁት ፈተናዎች ከአንድ በላይ መልስ ያላቸው ጥያቄዎች ታይተዋል፡፡

<u>ከ2005 ዓ.ም ፈተና፣</u>

ጥያቄ 15. "አንዱን ይዞ ሌላውን አንጠልጥሎ" የሚለው አነጋገር ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ከየትኛው ጋር አብሮ ይሄዳል?

A. ጭውውት C. ክርክር
B. ውይይት D. ቃለመጠይቅ

ትክክለኛው ምሳሌያዊ አነጋገር "አንዱን ይዞ ..." ሳይሆን "አንዱን ጥሎ..." ነው፡፡ ይህ ስህተት እንዳለ ሆኖ ሁሉም አማራጮች ከምሳሌያዊ አነጋገሩ ጋር አብረው አይሄዱም፡፡ የምሳሌያዊ አነጋገሩ መልእክት ሀሳብን በተገቢው መንገድ ከማቅረብ ይልቅ አንድን ርዕሰ ጉዳይ ጀምረው ሳይጨርሱ ሌላውን መቀጠልን ወይም መያዣ መጨበጫ የሌለውን ንግግር የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሁሉም አማራጮች ሀሳብን እዚህና እዚያ እያመሳቀሉ ማቅረብን ወይም መደበላለቅን አይፈቅዱም፡፡ ጭውውትም ቢሆን ሰዎች መንፈሳቸውን ዘና በማድረግ አንድን ርዕሰ ጉዳይ አንስተው የሚያከናውኑት የሀሳብ ልውውጥ እንጂ በምሳሌያዊ አነጋገሩ እንደተገለጸው ውል የሌለው ጉዳይ እየተዘባረቀ የሚቀርብበት አይደለም፡፡ ስለሆነም ለጥያቄው አንድ ትክክለኛ መልስ በአማራጭነት አልቀረበም፡፡

ጥያቄ. 40 ከሚከተሉት ቃላት ለየት የሚለው ቃል የትኛው ነው?

A. ሚሊኒየም C. ኮረንቲ
B. ባኞ D. ሠራዊት

ሌላው በ4.1.1 ሥር እንደተገለጸው ጥያቄ 40 ከጥያቄ ግልጽነት በተጨማሪ የአንድ ትክክለኛ መልስ መርህን አለሚሟላቱን ማስተዋል ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች

የተለያየ መነሻ ሀሳብ በመያዝ የተለያየ መልስ እንዲሰጡ ስለሚጋብዝ የጥያቄውን ትክክለኛነት ይጎዳዋል፡፡

<u>ከ2006 ዓ.ም ፈተና፣</u>

ጥያቄ. 1 የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ የሚጎድለው የሥርዐተ ነጥብ አይነት የቱ ነው?

A. ድርብ ሰረዝ
B. ነጠላ ሰረዝ
C. አራት ነጥብ
D. ትእምርተ አንክሮ

በምንባቡ የመጀመሪያ አንቀጽ ከአንድ በላይ ሥርአተ ነጥቦች ይጎድላሉ፡፡ ለአብነት " ቆይ ደግሞ እንገናኛለን" ለሚለው የዛቻ አገላለጽ ትእምርተ አንክሮ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም "... እየተጎማለለ እየፎከረ... እየዛተ እያስፈራራ ስፍራወን ለጥቢ ፀሐይ እየለቀቀ..." በሚሉት መዘርዝሮች መካከል የነጠላ ሰረዝ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከመሪ ጥያቄ ግልጽነት መጉደል የመነጨ ሁለት ትክክለኛ መልስ (B እና D) ሊኖሩት ችሏል፡፡

ጥያቄ 17. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ጭውውትንና ውይይትን የሚያመሳስላቸው የትኛው ነው?

A. ሁለቱም በማንም ሰው ሊጀመሩ ይችላሉ
B. ሁለቱም በተያዘ ቃለ-ጉባዔ ይቋጫሉ
C. ሁለቱም በሰላማዊ መንገድ ይመራሉ
D. ሁለቱም በዋና ጉዳይ ዙሪያ ያተኩራሉ

በዚህ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች C እና D መልስ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለዚህም የሁለቱን አማራጮች ባህሪ ማየት የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል፡፡ በምርጫ C በቀረበው መሰረት ጭውውትም ሆነ ውይይት በሰላማዊ መንገድ ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡ ከምርጫ D አንጻር ሁለቱም በዋና ጉዳይ ላይ አተኩረው ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ መነሻነት ከላይ የተገለጹት ሁለት አማራጮች መልስ መሆን ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በአማራጮች ውስጥ የታየውን አላስፈላጊ የቃላት ድግግሞሽ ለማስወገድ "ሁለቱም" የሚለውን ቃል በመሪ ጥያቄው ውስጥ ማቅረብ የተሻለ አቀራረብ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

ጥያቄ 24 ረዘም ባለ ምልልስ ላይ ተመስርቶ የቀረበ ነው፡፡ የሚፈለገው ምላሽም በስልክ ለተደረገው ምልልስ ላለመግባባታቸው ምክንያት የሆነውን እንዲመርጡ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አንጻር፣

ምርጫ A. ሐረገወይን የደወለላትን ሰው በድምጹ አለመለየቷ

ምርጫ C ሐረገወይን የደወለላትን ሰው ማንነት አለማወቋ

የሚሉት ሁለት አማራጮች ሐረገወይን፣ "አዎን ማን ልበል" እና "ይቅርታ ማን ልበል" በማለት ሦስት ጊዜ ከሰጠችው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ከሁለቱ አንዱን ብቻ ላለመግባባታቸው ምክንያት አድርጎ መቀበል አያስችልም፡፡ ስለሆነም የደወለላትን ሰው በድምጹ አለመለየቷ ወይም ማንነቱን አለማወቋ አለመግባባት እንደፈጠሩ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ የተነሣ ከላይ የቀረቡት ሁለት አማራጮች ትክክለኛ ምላሽ ይሆናሉ፡፡

### 4.1.2.3 "ሁሉም መልስ ናቸው" እና "ሁለም መልስ አይደሉም" የሚል አማራጮች ጥቅም ላይ ውለዋል?

በሦስቱ አመታት ፈተናዎች የቀረቡት 180 ጥያቄዎች ውስጥ "ሁሉም መልስ ናቸው" እና "ሁለም መልስ አይደሉም" የሚሉት በአማራጭነት አልቀረቡም፡፡ በዚህም ተገቢነት ያለው አቀራረብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 4.1.2.4 በትክክለኛው ምላሽና በአሳሳቾች መካከል በአጻጻፍ የጎላ የርዝመት ልዩነት ታይቷል?

ከዚህ መስፈርት አንጻር የሦስቱም አመታት ፈተናዎች ጉድለት አልታየባቸውም፡፡ በመሆኑም በአማራጮች አቀራረጽ ትክክለኛው መልስ ከአሳሳቾቹ ረዝሞ ባለመገኘቱ ለግምት ምላሽ ዕድል አይሰጥም፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማየት ይቻላል፡-

ከ2005 ዓ.ም ፈተና

ጥያቄ 36፣ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ትክክለኛ የቃላት አሰካክ ሥርዓት የሚታይበት አረፍተ ነገር የትኛው ነው?

A. ያለወቅቱ የሚጥል ዝናብ ለግብርና ሥራ አይበጅም

B. ያለወቅቱ የሚጥል ዝናብ በግብርና ሥራ አይበጅም

C. ያለወቅቱ የሚጥል ዝናብ የግብርና ሥራ አይበጅም

D. ያለወቅቱ የሚጥል ዝናብ ግብርና ሥራ አይበጅም

ጥያቄ 60፣ ከሚከተሉት ምሣሌያዊ አነጋገሮች መካከል ስለግለኝነት ወይም ስለራስወዳድነት የሚናገረው የትኛው አማራጭ ነው?

A. ከስስታም አንድ ያንቀወ አንድ ይወድቀው

B. ሁሉ ሄደ ተበተነ እህና እኔ ቀረነ አለ እያዘነ

C. ሆዴ ጀርባዬ ቢሆን ገፍቶ ገደል በከተተኝ

D. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ

ከ2006 ዓ.ም ፈተና

ጥያቄ 17፣ ከሚከተሉት መካከል ጭውውትንና ውይይትን የሚያመሳስላቸው የትኛው ነው?

A. ሁለቱም በማንም ሰወ ሊጀመሩ ይችላሉ

B. ሁለቱም በተያዘ ቃለ-ጉባዔ ይቋጫሉ

C. ሁለቱም በሠላማዊ መንገድ ይመራሉ

D. ሁለቱም በዋና ጉዳይ ዙሪያ ያተኩራሉ

ጥያቄ 22፣ “ቋጠረ” የሚለው ቃል “አጠራቀመ” የሚለውን ፍቺ የሚያስፈኘው ከሚከተሉት በየትኛው አረፍተ ነገር ውስጥ ባለው አገባብ ነው?

A. ሰወዬው ሳንቲሞቹን በመሐረቡ ጫፍ ቋጠረ

B. በእሳት የተለበለበው እግሩ ውሃ ቋጠረ

C. በንግዱም በእርሻውም እያለ ለቤቱ ደህና ገንዘብ ቋጠረ

D. ከክፍል ወጥቶ መሄድ ስለፈራ ሽንቱን ቋጠረ

ከ2007 ዓ.ም ፈተና፣

ጥያቄ 10፣ የአሸንዳ በዓል ለአሸንዳ ሴቶች የነፃነት ቀናቸው ነው የተባለው ለምንድነው?

A. የት ዋላችሁ ተብለው ስለማይጠየቁ

B. አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን ስለማያከብሩ

C. በየቤቱ እየጨፈሩ ስጦታ ስለሚያገኙ

D. ቡድን መስረትው ስለሚጨፍሩ

ጥያቄ 36፣ ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል ጥምር ቃል የያዘው የትኛው ነው?

A. የኢትጵያ አየር መንገድ አለም አቀፍ ስብሰባ አካሄደ፡፡

B. ትምህርት ቤት የዕውቀት ማፍሪያ ቦታ ነው፡፡

C. የከተማ አውቶቡስ ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

D. ጊዜን በከንቱ ማሳለፍ በዕድሜ መጫወት ነው፡፡

### 4.1.2.5 ፍጹም መለያ የሆኑ ቃላት በአሳሳቾቹ ውስጥ ተካተዋል?

ከዚህ የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አቀራረብ መርህ አንጻር በ3ቱ አመታት (2005-2007) ከተዘጋጁት ፈተናዎች ውስጥ በ2005 ዓ.ም፣ ጥያቄ 13 በምርጫ "A. ሁሉም ዓይነት ግጥሞች አንድ አይነት ምጣኔ አላቸው" እና በ2007 ዓ.ም ጥያቄ 19. በምርጫ "B. በአላማ የሚነበቡ ጽሑፎች በአንድ አይነት የንባብ ስልት ይመራሉ" እና በምርጫ "C. ማንኛውም የንባብ ስልት ፈተና ለማለፍ የሚደረግ የአነባብ ሥርዓት ነው" የሚሉት ፍጹም መለያ ቃላት በአማራጮቹ ውስጥ ተገኝተዋል፡፡

በእነዚህ አማራጮች እንደ የጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል "ሁሉም" ፣ "በአንድ ዓይነት" እና "ማንኛውም" የሚሉት ፍጹም መለያ ቃላት መገኘታቸው አሳሳቾቹን በቀላሉ ከአማራጭ ውጭ እንዲሆኑ ያደርጉዋቸዋል፡፡ በመጀመሪያው ጥያቄ አንድ አማራጭ እና በሁለተኛው ጥያቄ ሁለት አማራጮች በፍጹም መለያ መቅረባቸው የአማራጮቹን ብዛት ከአራት ወደ ሦስት እና ወደ ሁለት እንዲቀንሱ ያደርጋቸዋል፡፡ የጥያቄዎቹንም የመለካት አቅምና ትክክለኛነት ይጎዳል፡፡

### 4.1.2.6 አማራጮቹ ከላይ ወደታች የተደረደሩ ናቸው? ከመሪ ጥያቄው ጋርስ በተመሳሳይ ገጽ ላይ ቀርበዋል?

ሁሉም ጥያቄዎች ከነአማራጮቻቸው በተመሳሳይ ገጽ ላይ ቀርበዋል፡፡ የአማራጮቹ አደራደር ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አጫጭር ቅርጽ ያላቸው አማራጮች ከላይ ወደታች በሁለት ረድፍ የተደረደሩ ሲሆን ረዘም ያለ ቅርጽ ያላቸው አማራጮች አራቱም ከላይ ወደታች ተደርድረዋል፡፡ ይህም አደራደር ከመርሁ አንጻር ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን አቀራረቦች ማየት ይቻላል፡፡

<u>ከ2005 ዓ.ም ፈተና፣</u>

ጥያቄ 21፣ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ወይም ምስክርየሚናገረው የሚመዘግብ ይም የሚጽፍ ሰው ምን ይባላል? *(አጫጭር የአማራጮች ቅርጽ ላላቸው ጥያቄዎች ምሳሌ)*

A. ውል ተቀባይ  C. ትዕዛዝ ተቀባይ

B. ፍርድ ተቀባይ  D. ቃል ተቀባይ

<u>ከ2006 ዓ.ም ፈተና፣</u>

ጥያቄ 23፣ በቤተ መጽሐፍ ውስጥ የመጽሐፍት አጠቃቀም ሥርዓትን በተመለከተ ከሚከተሉት መካከል ልዩ የሆነው የትኛው ነው?
*(አጫጭር የአማራጮች ቅርጽ ላላቸው ጥያቄዎች ምሳሌ)*

A. መጽሐፍን ከተወሰደበት ቦታ በአግባቡ መመለስ

B. መጽሐፍ ስናነብ ባልተረዳነው ሐሣብ ስር ማስመር

C. መጽፍትን እንደራስ ንብርት አድርጎ መቁጠር

D. መጽሐፍትን በእንክብካቤ መያዝ

ከ2007 ዓ.ም ፈተና፣

ጥያቄ 12፣ የምንባቡ ይዘት ከሚከተሉት መካካል የትኛውን ያንጸባርቃል?
*(አጫጭር የአማራጮች ቅርጽ ላላቸው ጥያቄዎች ምሳሌ)*

A. ኢኮኖሚን  C. ማህበራዊ ኑሮን

B. ባህልን  D. ሃይማኖትን

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

ከ2005-2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ጥናቱ ከሚመለሳቸው ሁለት ቁልፍ ጥያቄዎች አንጻር ተገምግመው የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡

**ከመሪ ጥያቄ አቀራረብ አንጻር፣**

የምርጫ ጥያቄው ግልፅና ትርጉም ኖሮት ተፈታኙ እንዲረዳው በቂ መረጃ መስጠት አለበት፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ በመተከር ሊቀርብም ይገባዋል፡፡ ነገር ግን በጥያቄው ውስጥ የተደራረበ ነገር ሲኖር ተፈታኙን ግራ ስለሚያጋባ ጥያቄውን ለመመለስ ያስቸግራል፡፡ የሚዘጋጀውም የምርጫ ጥያቄ ግልጽና የማያሻማ ከሆነ ተፈታኙ ወደአማራጮቹ ከመሄዱ በፊት መልሱን እንዲለይ ይረዳዋል (ግሮንሉንድ፣ 1988፤ ብራውን፣ 1996) ፡፡ በመሪ ጥያቄ ውስጥ የሚቀርበው ችግር ግልጽና በቂ መረጃ መያዝ ሲገባው ይህን ያላሟሉ ጥያቄዎች በ 2005 ዓ.ም ሁለት ጥያቄዎች፣ በ2006 ዓ.ም ሦስት ጥያቄዎች፣ በ2007 ዓ.ም አንድ ጥያቄ በድምሩ 6 (10%) ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በ2005 ዓ.ም ከተዘጋጁት ጥያቄዎች 1 (1.67%) ጥያቄ በመሪ ጥያቄ ውስጥ የማያስፈልጉ ቃላት ተካተውበት ተገኝቷል፡፡

ግሮንሉንድ (1988)፣ ባችማን (1995) እና ዶውን ዚማሮ (2011) እንደሚያስረዱት በአዎንታዊ መልክ የተጻፉ የመልስ አስመራጭ ጥያቄዎች በአሉታዊ ሐረግ ከተጻፉት ጥያቄዎች በተሻለ ጠቃሚ የሆኑ የትምህርት አላማዎችንና ግቦችን ይለካሉ፡፡ በአሉታዊ ሐረግ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ለአጠያየቅ ቀላል በመሆናቸውና በፈተና ዝግጅት በቂ አሳሳቾች ለማቅረብ ሳይቻል ሲቀር ጥቅም ላይ የሚውሉ በመሆናቸው ተመራጭ አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄውን በአሉታዊ አቀራረብ መጠየቅ የግድ ከሆነ ለጥያቄው ትኩረት በመስጠት አሉታዊ ገላጭ የሆነው ቃል ወይም ሀረግ ተለይቶ በጉልህ መፃፍ ወይም ከስሩ መሰመር ይኖርበታል፡፡ ይህን መርሆ ከመጠበቅ አንጻር በ2007 ዓ.ም 2 (3.33%) ጥያቄዎች በመሪ ጥያቄው ውስጥ አሉታዊ ቃላትና ሐረጋት የተጠቀሙ ሲሆን ለቃላቱና ለሐረጋቱ ምንም ትኩረት እንዳልተሰጠውና በተለየ የአጻጻፍ ስልት እንዳልተጻፉ በግምገማው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ግሮንሉንድ (1988)፤ ብራውን (1996) እና ሃሊዲያናና ሌሎች (2011) እንደሚገልጹት በመሪ ጥያቄው ውስጥ ያለው ቃል ወይም ሀረግ በቀጥታ መልስ ሊሆን ከሚችለው አማራጭ

ጋር ከተገናኘና ፍንጭ ሰጪ የቃላት አጠቃቀም ካለ ተማሪው አሳሳቾችን ሳይመረምር በቀላሉ እንዲመልስ ያደርገዋል፡፡ ይህም በአሳሳች የቀረቡት አማራጮች ያላቸውን ፋይዳ ዝቅ ከማድረግ አልፎ የፈተናውን ትክክለኝነት ይጎዳዋል፡፡ ከዚሁ አንጻር በመሪ ጥያቄው ውስጥ ለትክክለኛው መልስ ፍንጭ ሊሰጡ የሚችሉ አገላለጾችን አስመልክቶ በ 2006 ዓ.ም 2 (3.33%) ጥያቄዎች እና በ 2007 ዓ.ም 1 (1.67%) ጥያቄ በድምሩ 3 (2.5%) ጥያቄዎች ችግሩ ታይቶባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በምንባብ፣ በመሪ ጥያቄ እና በአማራጮች ውስጥ በሦስቱም አመታት በተለያየ ደረጃም ቢሆን የሥርዓተ ነጥብ ችግር፣ የቃላት ግድፈትና የአጻጻፍ ወጥነት ችግር በግምገማው ታይቷል፡፡

**ከአማራጮች አቀራረብ አንጻር፣**

አሳሳቾች መልስ ሊሆን ከሚችለው አማራጭ ጋር የሚያቀራርባቸው ነገር እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡ ለፈተና ዝግጁ ያልሆኑ ተማሪዎችን እንዲያደናግሩ ስሕተት መልሶችን ትክክል የሚመስሉና የሚስቡ ማድረግ ተገቢ ነው ጥራት ያላቸውን ጥያቄዎች የማዘጋጀቱ ሚስጥር የሚወሰንወ ውጤታማ የሆኑ አሳሳቾችን ለየጥያቄው በመቅረጽ እንደሆነ ይታመናል (ግሮንሉንድ፣ 1988)፡፡ የአሳሳቾች አፃፃፍ ተፈታኙ ሊገባው በሚችል ቋንቋ ሆኖ አሳሳቾችና ትክክለኛው መልስ ተቀራራቢ የሆነ የመሳብ ሀይል ሊኖራቸው ይገባል (በርተንና ሌሎች፣ 1991)፡፡ ተገቢና ተአማኒነት ያላቸውን አሳሳቾች ከመቅረጽ አንጻርም በ 2005 ዓ.ም 2 (3.33%) ጥያቄዎች፣ በ 2006 ዓ.ም 4 (6.67%) ጥያቄዎች እና በ 2007 ዓ.ም 2 (5%) ጥያቄዎች በድምሩ 9 (6.67%) ጉድለት ታይቶባቸዋል፡፡ አንድ ትክክለኛ መልስ ወይም የተሻለ መልስ የሌላቸው በ 2005 ዓ.ም 2 (3.33%) ፣ በ 2006 ዓ.ም 4 (6.67%) ጥያቄዎች በድምሩ 6 (5%) ናቸው፡፡

ፍጹም መለያ የሆኑ ቃላትን በአማራጮች ውስጥ ሲካተቱ ተፈታኙ በቀላሉ እንዲያስወግዳቸው ይረዳዋል፡፡ ምክንያቱም ፍጹም መለያ የሆኑ ቃላት በአብዛኛው ከሐሰት ዐረፍተ ጀገረ ጋር የተዛመዱ ናቸው (ዳንኤል፣ 2006፤ ብራውን፣ 1994፤ ብሬም፣ 2013)፡፡ ከዚህ መርሆ አንጻር በ 2005 ዓ.ም ፈተና በአንድ ጥያቄ ከአማራጮቹ በአንዱ ውስጥ እና በ 2007 ዓ.ም ፈተና በአንድ ጥያቄ በድምሩ በ 2 (1.67%) ጥያቄዎች ከአማራጮቹ በሁለቱ ውስጥ ፍጹም መለያ የቃላት አጠቃቀም ተገኝቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፦ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ አቢይ ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከ 2005-2007 ዓ.ም ድረስ የተዘጋጁ የተከታታይ 3 ዓመታት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ የጥያቄ አቀራረብን (item format analysis) ከምርጫ ፈተና አዘገጃጀት መርሆዎች አንጻር መተንተን ነው፡፡ ጥያቄዎቹን ለመገምገም የሚረዱ ሁለት ቁልፍ ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ እነዚህም ቁልፍ ጥያቄዎች በመሪ ጥያቄ አጻጻፍ እና በአማራጮች አጻጻፍ ወይም አቀራረብ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ቁልፍ ጥያቄዎቹኑም ለመመለስ አስራሁለት መርሆዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በተጨማሪም በከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጁ የሦስቱ ዓመታት ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ የ8ኛ ክፍል ፈተናዎችን የጥያቄ ወረቀት በመረጃ ምንጭነት በመውሰድ የሰነድ ምርመራ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት የሚከተለው ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

- ከመሪ ጥያቄ አቀራረብ ጋር በተያያዘ ከ180 ጥያቄዎች ስድስት ጥያቄዎች ግልጽና በቂ መረጃ ያልያዙ ሆነው የተገኙ ሲሆን አንድ ጥያቄ ደግሞ የማያስፈልጉ የቃላት ክምችት ይዞ ተገኝቷል፡፡
- ከ180 ጥያቄዎች ውስጥ ምንም ዓይነት የትኩረት መለያ ሳይኖራቸው ሁለት ጥያቄዎች በመሪ ጥያቄው ውስጥ አሉታዊ የቃላት አጠቃቀም እንዲኖራቸው ተደርገው ተቀርጸዋል፡፡
- በመሪ ጥያቄው ውስጥ ለትክክለኛው ምላሽ ፍንጭ ሰጪ የሆኑ አቀራረቦች በሦስት ጥያቄዎች የታዩ ሲሆን በርካታ የአርትኦት ክፍተቶች በምንባቡ፣ በመሪ ጥያቄውና በአማራጮቹ ውስጥ ተገኝተዋል፡፡
- በዘጠኝ ጥያቄዎች ውስጥ የቀረቡት አሳሳቾች ተገቢነት የሌላቸውና ተአማኒነት የሚጎድላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም አምስት ጥያቄዎች አንድ ትክክለኛ መልስ ወይም የተሻለ መልስ (best answer) እንዲኖራቸው ሆነው አልተቀረጹም፡፡ ፍጹም መለያ ቃላትም በአንድ መሪ ጥያቄና እንዲሁም በሁለት አማራጮች ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

በሌላ መልኩ ከ2005-2007 ዓ.ም በሦስቱ አመታት በቀረቡት የከተማ አስተዳደሩ ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ጥያቄዎች በአማራጮቹ ውስጥ “ሁሉም መልስ ናቸው” እና “ሁለም

መልስ አይደሉም ወይም መልሱ አልተሰጠም" የሚሉት አቀራረቦች አለመታየታቸው የመልስ አስመራጭ ጥያቄ የፈተና መርሆን የጠበቀ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪም ለፈተና በቀረቡት የሦስት አመታት ጥያቄዎች ለግምት ምላሽ የሚያጋልጥ ከሁለት በላይ የትክክለኛ መልሶች ክትትል አልተስተዋለም፡፡ ይህም የትክክለኛ መልሶች አቀማመጥ መርህን የተከተለ እንደሆነ ከግምገማው ውጤት መረዳት ይቻላል፡፡

በሦስቱ አመታት (ከ2005-2007 ዓ.ም) በቀረቡት ፈተናዎች በአማራጮቹ ውስጥ ለትክክለኛ ምላሽ ግምት የሚያጋልጥ የአፃፃፍ ርዝመት ባለመስተዋሉ ከመርሁ አንጻር ተገቢ አቀራረጽን የጠበቀ ነው፡፡

መሪ ጥያቄውና አማራጮቹ በአንድ ገጽ ላይ የቀረቡ ሲሆን የአማራጮች አደራደርም ተገቢውን የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አዘገጃጀትና አቀራረብ የተከተለ ነው፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው ከ2005-2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው ለፈተና ከቀረቡት 180 የአማርኛ ቋንቋ ጥያቄዎች በአብዛኛው የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አዘገጃጀት መርሆዎችን ተከትለው የተዘጋጁ ቢሆኑም ጉድለት የታየባቸው ጥያቄዎች ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱ በተማሪዎች ውጤት ላይ ጉዳት ማስከተላቸው አይቀሬ ነው፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አዘገጃጀት መርሆዎችን ጠብቆ የተዘጋጀ የቋንቋ ፈተና ተማሪዎችን በትክክል ሊለካ ስለሚያስችል የሚመዘገበውም ውጤት አስተማማኝነት እና ተገቢነት እንዲኖረው የሚያደርግ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ከዚህ አንጻር ከ2005-2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተዘጋጅተው ለፈተና የቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ጥናቱ ይዞ ከተነሳቸው ቁልፍ ጥያቄዎች አንጻር የሚከተሉት ድምዳሜዎች ተሰጥተዋል፡፡

በመገምገሚያ መርሆዎቹ መሰረት "ሁሉም መልስ ናቸው" እና "ሁለም መልስ አይደሉም" የሚሉ አማራጮች ጥቅም ላይ አለመዋላቸው፣ በትክክለኛው ምላሽና በአሳሳቾች መካከል በአጻጻፍ የጎላ የርዝመት ልዩነት አለመታየቱ፣ አማራጮች ከመሪ ጥያቄው ጋር በተመሳሳይ

ገጽ ላይ መቅረባቸው እና አደራደራቸውም ከላይ ወደታች መሆኑ በአዎንታዊነት የሚጠቀሱ የአማራጮች አቀራረቦች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የመልስ አስመራጭ ጥያቄ አዘገጃጀት መርሆዎችን ያልጠበቁ ጥያቄዎችም ተገኝተዋል፡፡ በመሪ ጥያቄው ውስጥ ግልፅና በቂ መረጃ ያልያዙ፣ አሉታዊ ቃላትን በመጠቀም የቀረቡ፣ ጉልህ ፍንጭ ሲጪ የያዙና በአፃፃፍ ስልት ወጥነት የጎደላቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በተመሳሳይ ከአማራጮች አቀራረብ አንጻር በውስጣቸው ሳቢነትና ተአማኒነት የጎደላቸው አሳሳቾችን ማካተታቸው፣ ከቀረቡት አማራጮች አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲኖራቸው ሆነው ያልተዘጋጁ መኖራቸውና በተወሰኑ አማራጮች ውስጥ የፍጹም መለያ ቃላት መገኘታቸው እንደችግር ተስተውሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሦስቱም አመታት ፈተናዎች በምንባብ፣ በመመሪያዎችና በአማራጮች ውስጥ በርካታ የአርትኦት ችግሮች ታይተዋል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው ከ2005-2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥያቄ መርሆዎችን ተከትሎ በአብዛኛው የተዘጋጀ ቢሆንም በ2005 ዓ.ም 9 (15%)፤ በ2006 ዓ.ም 18 (30%)፤ በ2007 ዓ.ም 10 (16.67%) ጥያቄዎች በድምሩ በተገመገሙት የሦስት አመታት ፈተናዎች ውስጥ 37 (20.56%) ጥያቄዎች ችግር ታይቶባቸዋል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ፈተናውን በባለቤትነት የሚመራው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶች መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች ግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊውን ክትትል ቢያደርግ የፈተናውን ጥራት ለማስጠበቅ እንደሚያስችለው ይታመናል፡፡

- የተገመገሙት የሦስት አመታት ጥያቄዎች ክልላዊ ፈተና ከመሆናቸው አንጻር በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች የሚወስዱት ፈተና መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም መሪ ጥያቄው ሲቀረጽ ግልጽና ሊጠየቅ የተፈለገውን ጉዳይ ሳያድበሰብስ ማቅረብ እንደሚኖርበት የዘርፉ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ከዚህ አንጻር በጥናቱ የተገኙትና በመሪ ጥያቄ ዝግጅት የታዩት ጉድለቶች በፈተና

አስተማማኝነትና በተፈታኞች ውጤት ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢው ጥንቃቄ ቢደረግ፣

- የታዩት የአሉታዊ ቃላት አጠቃቀም ችግሮች ትኩረት በመስጠት አሉታዊ ቃለቱን መጠቀም የግድ የሚል ከሆነ ቢያንስ በተለየ የአጻጻፍ ስልት በማቅረብ ተገቢው አትኩሮት እንዲሰጣቸው ቢደረግ፣
- ለግመታ የሚያጋልጡ ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሐረጎችን ባለመጠቀም ተማሪዎችን በትክክል ሊለኩ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቢዘጋጁና ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የአርትዖት ሥራ በጥንቃቄ መሥራት ቢቻል፣
- በመልስ አስመራጭ ጥያቄ ዝግጅት ወቅት ዋነኛው በትኩረት ሊሰራ የሚገባው ሳቢነት ያላቸው አሳሳቾችን መቅረጽ ነው፡፡ ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በዘጠኝ ጥያቄዎች ውስጥ የአሳሳችነት ተግባራቸውን በትክክል የማይወጡ አማራጮች ታይተዋል፡፡ በተጨማሪም አንድ ትክክለኛ መልስ ወይም የተሻለ መልስ (best answer) ያልያዙ አማራጮች በአምስት ጥያቄዎች ውስጥ ታይተዋል፡፡ ስለሆነም የፈተናን የጥያቄ አቀራረብ ብቃት ለማሻሻል ይቻል ዘንድ ፈተናው ለተፈታኞች ከመቅረቡ በፊት በባለሙያዎች በቂ ፍተሻ ማስደረግ ጠቃሚ ይሆናል፡፡
- ፍጹም መለያ ቃላትና ሐረጋትን መጠቀም አሳሳቹን በቀላሉ በመለየት ከምርጫ ውጪ እንዲሆን ዕድል ይሰጣል፡፡ ስለሆነም የመልስ አስመራጭ ጥያቄን ብቃት ከፍ ለማድረግ እንደነዚህ አይነት ቃላትና ሀረጋትን ከአማራጮች ውስጥ በማስወገድ የአሳሳቾችን ሚና ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

Alderson, J. C.; Claphan.C and Wall.D. (1995). *Language Test Construction and Evaluation.* Great Britain: CUP

Bachman, L.F. (1990). Fundamental Consideration in Language Testing. Oxford : oxford University press.

___________. (1995). *Fundamental Considerations in Language Testing.* Oxford: Oxford University Press.

Baker ,D.(1989). *Languge Testing. Acritical survey & practical Guide* . London: Edward Arnold.

Brame, J.C.(2013).*Writing Good Multiple Choice Test Questions*. https:// cft.vanderbitt. edu/guide-sub-pages.

Brain Tomlinson. (2005). *Testing to learn: a personal view of language testing*. ELT Journal V.59/1 January 2005, PP.39-46: Oxford University Press.

Brown, J. D. (1996). *Testing in Language Programs*. New Jercy: Prentice Hall Rejents.

Brown, H. D (1994). *Principles of language learning and teaching.* London:Hall International (UK ) limited.

___________. (2004). *Language Assessment Principles and Classroom Practices.* New York: Pearson Education, Inc.

Burton, S.J, Sudweeks, R.R., Merrill, P.F., and Wood Bud (1991). *How to Prepare Multiple-Choice Test Items: Guidelines for University Faculty*. Bringham Young Univesty Testing Services.

Chan.Y.F. & Kaur.G.S.(2013). *Assessment practices in higher education in United States.* Procedia Social and Behavioral Sciences፡ Elsevier Ltd.

Clay .B. (2001). *Is This a Trick Question? A Short Guide to Writing Effective Test Questions*፡ Kansas Curriculum Center.

Clegg,V.L. and Cashin, W.E. (1986). *Improving Multiple-Choice Tests*: Kansas State University.

Ebel, Robert L.and Fersbie, David A. (1991). *Essentials of Educational Measurement* (5th ed.) New Delhi: PHI learing private limited.

Ellsworth,R.A.; Dunnel,P, and Duell,O.K. (1990). *Multiple Choice Test Items: What Are Textbook Authers Telling Teachers*? The Journal of Eductional Research, 83(5), 289-293.

Green, A. (1998). *Principles of Language Testing*. Sajunga: Bendrasu Program Documents.

Gronlud, N. E. (1968). *Construction Achivement Tests.* USA: Prentice Hall, Inc.

___________ . (1981). Measurement and Evaluation in Teaching. 4th ed. NewYork: macmilan.

___________. (1988).*How to construct Achivement Tests*. Englewood cliffs,New Jrseye: printce-hall,Inc.

___________. (2003). *Assessment of Student Achievement (7 ed).* Boston: Pearson Education, Inc.

Haladyna, T. M. and Downing, S. M. (1986). *Functional Distractors*. Implications for Test-Item Writing and Test Design.http://www.sagepub.com/journals.nav.Eric, (pp 1-20)

___________. (1989a). *A Taxonomy of Multiple-choice Item-writing Rules*. APPLIED MEASUREMENT IN EDUCATION, 1,37– 50: Lawrence Erlbaum Associates, Inc.

Haladyna, T.M.; Downing, S. M.. and Rodriguez, M.C (2002). *A Review of Multiple Choice Item-Writing Guidleines of Classroom Assessment*. Hillsdale: Laweerence Erlbaum Associate, Inc.

Harrison, A. (1983). *A Language Testing Hand book*. London: Macmillan publishers.

Heaton. J.B. (1975). *Writing English Language Tests*. Londen: long man.

___________. (1988).*Writting English Language Tests*,(second ed.)Harlow:Longman.

___________. (1990). *Writing English Language Tests.* New York: Longman Inc.

Hubbred and Others. (1983). *A Testing Language Teachers*. Cambridge: C.U.P.

Huges, A. (1992). *Testing for Language Teachers*. Great Britain: CUP.

___________. (2003). *Testing for Language Teachers*. Second Edition. Cambridge:CUP.

Mullis. V.S. and Martin. O. M. (2011). *ITEM WRITING GUIDELINES*. TIMSS & PIRLS: International Study Center Lynch School of Education, Boston college.

Richards,J.C (1998). *The Context of Language Testing*. Cambridge University Press.

Rodriguez, C. M. (August,1977). *The Art & Science of Item Writing*: A Meta-Analysis of Multiple-Choice Item Format Effects. Chicago: www. edmeasurment. net/aera/ artandscience. pdf.

Stephn Andrews. (2004). *WASHBACK IN LANGUAGE TESTING: Washback and Curriculum Innovation*. Lawrence Elbaum Associates, Inc.Mahwah, New Jercy.

Tanner, D.E.(2003). *MULTIPLE-CHOICE ITEMS: PARIAH, PANACEA, or Neither of the Above?* American secondary Education, v.31, No 2. PP.27-36: Dawight Schar Colledge of Education, Ashland Universty.

Zimmaro. D. M. (2004). *Writing Good Multiple-Choice Exams*. Measurement and Evaluation Center፡ Web: www.utexas.edu/academic/mec.

ባንችዓምላክ ፀጋዬ፡፡ (2002)፡፡ የ2001 ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና የይዘት ትክክለኛነት ብቃት ትንተና፡፡ ለማስተር ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ በህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ፡፡

ትንሳኤ ብርሃኔ፡፡ (1988) (እ.ኢ.አ)፡፡ የአማርኛ ቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የ፪ኛ ዲግሪ ማሟያ፣ ያልታተመ፡፡

ቅጣው ስለሺ፡፡ (2007) (እ.ኢ.አ)፡፡የ2006 ዓ.ም የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተና ብቃት /item format/ ግምገማ፡፡ ለማስተር ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ በህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ፡፡

አገኘሁ ተስፋ፡፡ (2005) (እ.ኢ.አ)፡፡ *በኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በማስተማር ዝግጅትና ትግበራ ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ የመምህራን ግንዛቤ፡፡* የአማርኛ ቋንቋና ባህል ዘርፎች ፩ኛው አገር አቀፍ አውደ ጥናት መድብል፡፡ ባህር ዳር፣ ፖሊ ፔዳ ማተሚያ ቤት፡፡ (ገጽ 114-137)፡፡

ዳንኤል ዘውዴ፡፡ (2006) (እ.ኢ.አ)፡፡ በክፍል ምዘና አተገባበር ተጨባጭ ስልቶች፡፡ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

## ማረጋገጫ

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ያዘጋጀሁት እኔ መሆኔን እያረጋገጥሁ ማንኛውም ሀሳብ፣ እውነታና የመረጃ ምንጭ ማዛባት፣ የፈጠራ ስራ በመጨመር ሙያዊ ታማኝነትና ሀቀኝነትን ማጉደል በዩኒቨርስቲው የዲስፒሊን እርምጃ እንደሚያስወስድና ምንጮችን በትክክል አለመጥቀስ እንደሚያስጠይቅ ጥብቅ እምነት አለኝ፤ በመሆኑም በዚህ ጥናት የተጠቀምኩባቸው ድርሳናት ዋቢነታቸው በትክክል የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

-----------------------------------------------

ፊርማ

-----------------------------------------------

የተማሪው ስም

-----------------------------------------------

የመታወቂያ ቁጥር

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የተጠናቀቀ በመሆኑ ለፈተና እንዲቀርብ ተስማምቻለሁ፡፡

-----------------------------------------------

ፊርማ

-----------------------------------------------

የአማካሪ ስም

-----------------------------------------------

ቀን